
# የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ

# 8ኛ ክፍል



የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር

# ለመጽሐፉ ሊደረግ ስለሚገባው የአያያዝ ጥንቃቄ




ይህን መጽሐፍ ብዙ ተማሪዎች ስለሚገለገሉበት በጥንቃቄ ሊያዝ ይገባዋል፡፡ የሚከተሉት 10 ነጥቦች መጽሐፉን በጥንቃቄ ይዞ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ሃሳብ ይሰጣሉ፡፡

1. የመጽሐፉን ሽፋን በጠንካራ ወረቀት ወይንም በላስቲክ መሸፈን፡፡
2. መጽሐፉን ርጥበት በሌለበት ደረቅ ቦታ ላይ በጥንቃቄ ማስቀመጥ፡፡
3. መጽሐፉን በቆሻሻ እጅ ያለማገላበጥና ገፆቹን ያለመግለጥ፡፡
4. በመጽሐፉ የሽፋንም ሆነ የውስጥ ገፆች ላይ አላስፈላጊ የሆኑ ስዕሎችንና ጽሑፎችን ያለመሳልና ያለመጻፍ፡፡
5. ለመጽሐፉ የገጽ መለያ ወይንም የንባብ ማረፊያ የሆነ እልባት በጠንካራ ክርታስ ሠርቶ መጠቀም እንጂ የቆሙበትን ቦታ ለማስታወስ ገፆቹን ደጋግሞ ያለማጠፍ፡፡
6. ከመጽሐፉ ውስጥ አንድም ገጽ ሆነ ስዕል ገንጥሎ አለማውጣት፡፡
7. መጽሐፉ ቢገነጠል እንኳ በጥንቃቄ መልሶ በማጣበቂያ ማስተሸ ማያያዝ፡፡
8. መጽሐፉ ቦርሳ ውስጥ ሲከተት እንዳይታጠፍና እንዳይጨማደድ ጥንቃቄ ማድረግ፡፡
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው በውሰት ሲሰጥ የተዋሰው ሰው በጥንቃቄ እንዲይዝ መንገር፡፡
10. መጽሐፉን በጥንቃቄ መግለጥ፣ ገፆቹ እንዳይገነጠሉና እንዳይወይቡ በጥንቃቄ መያዝ፡፡

# የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ

## 8ኛ ክፍል


አዘጋጅ፡- ፕሪን ኢንተርናሽናል አማካሪ ድርጅት

ጸሐፊ፡- አቶ ጳውሎስ ካሱ

የቴክኒካል አማካሪዎች፡- ዶ/ር ተስፋዬ ባሻ፣ አቶ አንድአርጋቸው ደነቀ

አርታኢ፡- አቶ የሻው ተሰማ

ግራፊክስ ዲዛይን፡- አቶ ፍቃደእግዚአብሄር ከበደ

የምልክት ቋንቋ ስዕል፡- አቶ ካሌብ በለጠ

ሌሎች ስዕሎች፡- አቶ አሰፋ ጉታ

አስተባባሪዎች፡- ዶ/ር ጥላዬ ካሣሁን፣ ዶ/ር ተስፋዬ ባሻ፣ አቶ አንድአርጋቸው ደነቀ



የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር

# ማውጫ


መግቢያ ———— 3

ምዕራፍ አንድ:

የሥራ ፍቅር ———— 9

ምዕራፍ ሁለት፡

ባህላዊ ቅርሶች ———— 17

ምዕራፍ ሦስት፡

ሰበአዊ መብቶች ———— 25

ምዕራፍ አራት፡

የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ———— 32

ምዕራፍ አምስት፡

የታዋቂ ሴቶች የሕይወት ታሪክ ———— 39

ምዕራፍ ስድስት፡

በረሐማነት ———— 48

ምዕራፍ ስባት፡

መከባበር ———— 56

ምዕራፍ ስምንት፡

ወጣትነት ———— 64

ምዕራፍ ዘጠኝ፡

የአየር ንብረት ለውጥ ———— 72

ምዕራፍ አስር፡

የሀገር ፍቅር ———— 79

## መግቢያ

ይህ የመምህሩ መምሪያ የተዘጋጀው የኢምቋ ትምህርት የሚሰጥባቸውን ስድስት አቀራረብ ደረጃዎች መሠረት አድርጎ ነው፤

1. *የምልክቶቹን አሠራር ማሳየት፡-* መምህራን ወደ ክፍል ከመግባታቸው በፊት ለዕለቱ ትምህርት የሚያስፈልጉትን ምልክቶች ሁሉ መለማመድ አለባቸው፡፡ ከምንባብም ሆነ ከመልመጃዎች በፊት ለተማሪዎቹ ቁልፍ ምልክቶችን ማሳየት ያስፈልጋል፡፡ ይህም ተማሪዎቹ የትምህርቱን ሂደት በቀላሉ ለመከታተል ይረዳቸዋል፡፡

2. *የምልክቶቹን የጣት ፊደላት ማሳየት፡-* ተማሪዎቹ የምልክቶቹን አሠራር በሚገባ ከተረዱ በኋላ፣ ምልክቶቹን የጣት ፊደላት እንዲያውቁ መርዳት ምልክቶቹ በጽሑፍ በሚቀርቡበት ጊዜ በቀላሉ ለመረዳትና ሐሳባቸውንም ያለ ብዙ ውጣ ወረድ በጽሑፍ ለመግለጽ ይረዳቸዋል፡፡

3. *ማብራራት፡-* ተማሪዎቹ ምልክቶቹን በማየትና የጣት ፊደሎችን ብቻ በመመልከት ጽንሰ ሐሳባቸውን ላይረዱ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ መምህራን ምልክቶቹ የሚወክሉትን ጽንስ ሐሳብ ማብራራት አለባቸው፡፡

4. *ምልክቶቹን በምንባብና በመልመጃ ውስጥ መጠቀም፡-* የሚቀጥለው የሂደት ደረጃ ምልክቶቹን በመልመጃዎችና በምንባብ ውስጥ እንደ አገባባቸው በማሳየት ተማሪዎቹ ስለአገልግሎታቸውና ትርጉማቸው ሰፋ ያለ ዕውቀት እንዲያገኙ መርዳት ነው፡፡

5. *ተማሪዎቹ ምልክቶቹን እንዲጠቀሙ ማድረግ፡-* ይህ በኢምቋ ትምህርት ውሰጥ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም ከሌሎች ትምህርቶች በተለየ ሁኔታ የኢምቋ ትምህርት በዋናነት መከናወን ያለበት በክፍል ውስጥ በመሆኑ ነው፡፡ ምልክቶቹ የሕይወታቸው አካል እንዲሆኑ፣ ተማሪዎቹ ምልክቶቹን በመልሶቻቸው፣ በክፍል ውስጥ ውይይቶች፣ በክርክር፣ ወዘተ በተግባር እንዲጠቀሙባቸው ሰፋ ያሉ ዕድሎች ማመቻቸት በአምስተኛ ደረጃ የሚመጣበት ጉዳይ ነው፡፡

6. *መከለስ፡-* በስድስተኛ ደረጃ ላይ ሲደረስ፣ ምልክቶቹ በተማሪዎቹ ውስጥ እንዲሰርጹ ከማናቸውም የክፍል ውስጥ ተግባራት በፊት ቁልፍ ምልክቶችን እንዲሁም እስከዛ ደረጃ ድረስ ጥቅም ላይ የዋሉ ምልክቶችን ሁሉ መከለስ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

አስፈላጊ ዝግጅቶች፡-

ርእሱን የሚያሳዩትን ምልክቶች ከፊት ገለጣቸውና አካላዊ እንቅስቃሴያቸው ጋር በሚገባ መለማመድ፤

- *ሥዕሉን አጥንቶ የያዛቸውን መልእክቶች ዝርዝር ማዘጋጀትና በኢምቋ መለማመድ፣*
- *ምንባቡን በጥንቃቄ ማንበብና ወደ ኢምቋ ቀይሮ መለማመድ፣ ለዚህ ተግባር ከየምዕራፉ ምንባብ ውስጥ ተወስደው በየምዕራፉ መጨረሻ ላይ የተሰጡትን የኢምቋ ናሙና ሰዋሰው ሥርአቶች እንደመመሪያ መጠቀም ይመከራል፡፡*

- *የምንባቡን መልዕክት በአጭሩ በኢምቋ ማዘጋጀት፣*
- *ከምንባቡ ውስጥ ተማሪዎቹ ቀደም ባሉት ክፍሎች ውስጥ የተማሯቸውን ምልክቶችና ሊማሯቸው የሚገቡ ምልክቶችን ዝርዝር ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ በመቀጠልም ቀደም ሲል የተማሯቸውን በክለሳ ብቻ በማለፍ አዳዲሶቹን ምልክቶች በተማሪዎቹ ውስጥ እንዲሰርጹ ምዕራፉ ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ በየክፍለ ጊዜው አገልግሎት ላይ የሚውሉበትን መንገድ ማቀድና ተግባራዊ ማድረግ ይመከራል፡፡ እንዲሁም የምልክቶቹን ክፍሎች ትነተናዎች ማዘጋጀትና ለተማሪዎቹ ማለማመድ ያስፈልጋል፣*
- *የተሰጡትን ጥቂት ምስላዊ ምሳሌዎች መሠረት በማድረግ የግሶችን አጠቃቀም መለማመድና በክፍሉ ውስጥ ጥሩ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ምልክቶችን ማዘጋጀት፤*
- *የቡድን ውይይቱንና ክርክሩን ውጤታማ የሚያደርጉ ዘዴዎች ማዘጋጀት አስፈላጊ ይሆናል፡፡*

## አስፈላጊ የትምህርት መርጃዎች

የኢምቋ መምህራን ለመርጃ መሣሪያዎች ከፍተኛ ትኩርት መስጠት አለባቸው፡፡ ምክንያቱም የኢምቋ የዕይታ ቋንቋ ስለሆነ መርጃ መሣሪያዎች ቁልፍ ሚና አላቸው፡፡ በኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሄራዊ ማኅበር የታተመው የኢምቋ መዝገበ ምልክት ሁልጊዜም የማይለያቸው ዋንኛው መርጃ መሣሪያ ተደርጎ መወሰድ አለበት፡፡ በተጨማሪም  መምህራን ፎቶ ግራፎችን እራሳቸው እያነሱ መጠቀም ይችላሉ፡፡ ሥዕሎች፣ ፎቶግራፎች፣ ተንቀሳቃሽ ፊልሞች፣ ካርቱኖች  ወዘተ፣ እንደተገኙ አገልግሎት ላይ ለማዋል መሞከር አለባቸው፡፡ መምህራን የምዕራፉን ቁልፍ ምልክቶችና ወካይ ሥዕላቸውን ወይም ፎቷቸውን ካልተቻለም የጽሁፍ አቻቸውን በተቃራኒ ገጾቻቸው የያዙ ካርዶች በግላቸው በማዘጋጀት መጠቀም አለባቸው፡፡

## ርእሶችን ማስተዋወቅ፡-

- *ከማኛውም ትምህርት በፊት ርእሱን ማስተዋወቅ፡ ሐሳቡ ግልጽ እስኪሆንላቸው ድረስ ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡*

## የመልመጃዎች  አሠራር ሂደት፡-

1. *የሚከተሉትን ጉዳዮች በጥቁር ሰሌዳው ላይ መጻፍ*
   - የምዕራፉን ዋና ርእስ፡
   - የመልመጃውን ርእስ፡
   - ከርእሱ ጋር የተያያዙ ቁልፍ ምልክቶች ወካይ ቃል

2. *ማሳየት፡-*

- በጥቁር ሰሌዳው ላይ የተጻፉትን ወካይ ቃላት ምልክቶች ማሳየት

3. *ማስረዳት፡-*

- የምልክቶቹን ወካይ ቃላት የጣት ፊደላት ማሳየት
- የምልክቶቹን ጽንሰ ሐሳብ ማስረዳት

4. *መልመጃውን ማስተዋወቅ፡-*

- መመሪያውን ለተማሪዎቹ አንብቦ የሚጠበቀውን ተግባር ማስረዳት

5. *ውይይት፡-*

- ተማሪዎቹ ሥዕሉን እንዲያጠኑ ከ2-3 ደቂቃ መፍቀድ
- ተማሪዎቹ ሥዕሉን እንዲያስረዱ ማበረታታት
- ተማሪዎቹ መልስ ሲሰጡ የምልክቶች አጠቃቀማቸውን እየተከታተሉ አስፈላጊውን እረማት መስጠት
- ተማሪዎቹ አዳዲስ ምልክቶች ሲጠቀሙ በጥቁር ሰሌዳው ላይ መጻፍ

6. *አጭር ማብራሪያ፡*

- ተማሪዎቹ እንዲጠቀማቸው የታቀዱትን ምልክቶችና የቋንቋ ክፍሎች በመጠቀም ሥዕሉምን እንደሆነ ማብራራት
- በቁጥር አንድ ስር በተሰጠው መመሪያ መሠረት በጥቁር ሰሌዳው ላይ የተጻፉትን የምልክቶች ወካይ ቃላት እና ተማሪዎቹ የተጠቀሟቸውን አዳዲስ ምልክቶች ማብራራት

7. *የተማሯቸውን ምልክቶች ተጠቅመው የራሳቸውን ሐሳብ መግለጽ እንዲችሉ ማለማመድ፡-*

- ተማሪዎቹ በዕለቱ የተማሯቸውን ምልክቶችና አጠቃቀማቸውን በመጠቀም የራሳቸውን ሐሳብ እንዲያስረዱ ሰፋ ያለ ዕድል ማመቻቸት አስፈላጊ ነው

8. *ክለሳ፡-*

- በእያንዳንዱ ክፍለጊዜ መጨረሻ ላይ በጥቁር ሰሌዳው ላይ የተጻፉትን ወካይ ቃላት ምልክቶች ከተማሪዎቹ ጋር መከለስ አስፈላጊ ነው

9. *ግምገማ፡-*

- ተማሪዎቹን ተራ በተራ በጥቁር ሰሌዳው ላይ የተጻፉትን ምልክቶች እንዲያሳዩ መጠየቅ

- በዕለቱ ከተማራቸው ምልክቶቹ ውስጥ የቻሉትን ያህል የምልክቶች ብዛት በመጠቀም በክፍል ውስጥ ዐረፍተ ነገሮች እንዲሠሩ ማበረታት
- ውይይት፣ ክርክር፣ ወዘተ፣ በመጠቀም ተማሪዎቹ ጅምሮቻቸውን እንዲያስፋፉ ማበረታታት።

የምንባብ አጠቃቀም፡-

- *ወደ ክፍል ከመምጣት በፊት ምንባቡን አንብቦ ትኩረት የሚገባቸውን ምልክቶች መለየት*
- *ምልክቶቹን መለማመድ*
- *ምንባቡን በኢምቋ ማቅረብ የሚቻልበትን መንገድ መለማመድ*
- *ቀደም ብለው የተዘጋጁትን የምንባቡን ቁልፍ ምልክቶች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጽፎ አሠራራቸውን ማሳየት፣ ጽንሰ ሐሳባቸውን ማስረዳት*
- *ለቁልፍ ምልክቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት፣ ምንባቡን ለተማሪዎቹ ማንበብ*
- *የምንባቡን ሐሳብ በኢምቋ ማቅረብ*
- *ተማሪዎቹ ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች እንዲጠይቁ ማበረታታ*
- *ተማሪዎቹ ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ትምህርት ዝግጅት ምንባቡን በግላቸው አንበበው እና በኢምቋ እንዴት መቅረብ እንዳለበት ተለማምደው እንዲመጡ ማባረታታት*

የመልመጃዎች ትግበራ ሂደት፡

- *ቁልፍ ምልክቶችን በሰሌዳው ላይ ጽፎ ማሳየት፣ ማስረዳት*
- *መመሪያውን ለተማሪዎቹ አንብቦ ማስረዳት*
- *ጥያቄዎቹን አንድ በአንድ በማንበብ ምን ማለት እንደሆነ ማስረዳትና ተማሪዎቹ ብዙ ምልክቶችን፣ የተለያዩ የዐረፍተ ነገር አወቃቀሮችን እንዲሁም አንድን ሐሳብ መግለጽ የሚቻልባቸውን የተለያዩ መንገዶች የማየት ዕድል እንዲያገኙ ለእያንዳንዱ ጥያቄ እስከ ሦስት የሚደርሱ ተማሪዎች መልስ እንዲሰጡ ማድረግ*
- *ተማሪዎቹ መልስ ሲሰጡ አስፈላጊውን እርማትና ድጋፍ ማድረግ*
- *ተማሪዎቹ መልስ ሲሰጡ ከተቻለ በቪድዮ ካሜራ መቅረጽ። ይህ ካልተቻለ ተማሪዎቹ ቀደም ሲል በክፍል ውስጥ ያልተነሱ ምልክቶችን ከተጠቀሙ ወካይ ቃሎችን በጥቁር ሰሌዳው ላይ መጻፍ*
- *ከተማሪዎቹ መልሶች ውስጥ ናሙና ዐረፍተ ነገሮች በሰሌዳው ላይ በመጻፍ*

- *ጥያቄና መልሱ እንደተጠናቀቀ በሰሌዳው ላይ በተጻፉት ቃላት/ምልክቶችና ዐረፍተ ነገሮች ላይ በመወያየት የተማሪዎቹ የኢምቋ ክሂል እንዲያዳብሩ መርዳትና በሚቀጥሉት ትምህርቶች ውስጥ በግብአትነት መጠቀም፡፡*

## የውይይት አጠቃቀም

የውይይት ዓላማ፤

- *ተማሪዎቹ እርስ በርስ እንዲማማሩ መርዳት*
- *ተማሪዎች እርስ በእርሳቸው በሚነጋገሩበት ጊዜ ተፈጥሮአዊ የኢምቋ ስለሚጠቀሙ ለመምህሩ የኢምቋ ተፈጥሮአዊ አጠቃም የማየት ዕድል መፍጠር ነው፡፡*
- *ቀደም ሲል የተጀመሩ ጅምሮችን ለማስፋት የሚችሉባቸውን ዕድሎች ማመቻቸት ነው፡፡*

ክንውን፡

- *እንደ ክፍሉ ብዛት ተማሪዎቹን ከአራት እስከ አምስት አባላት ባቀፉ ቡድኖች መከፋፈል፣*
- *መምህር አንድ ጥያቄ ለአንድ ቡድን በማንበብ ከአብራሩ በኋላ ከ10 እስከ 15 ደቂቃ ሰጥቶ የቡድን ውይይቱን እየተዘዋወሩ መከታተል፣*
- *በውይይቱ መጨረሻ ላይ ከቡድን አባሎቹ አንዱ ከተማሪዎቹ ፊት ቆሞ የቡድን ውይይቱን ውጤት እንዲያቀርብ ማበረታታት፡፡*

## የትረካ አጠቃቀም

- *የትረካ ዓላማ ተማሪዎቹ የተረዱትን በራሳቸው መንገድ መልሰው በማስረዳት የአረዳድ ሁኔታቸውን እንዲያሳዩና እግረ መንገዳቸውንም የንግግር ችሎታቸውን እንዲያደብሩ መርዳት ነው፡፡ መምህራን ትረካውን ይህ ክሂል ሊዳብር በሚችልበት መንገድ ማመቻቸት አለባቸው፡፡*
- *በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት ነጥቦች በተማሪዎቹ ትረካ ውስጥ መካተታቸውን መከታተልና አስፈላጊውን እርማትና ድጋፎች ማድረግ*
- *የተማሪዎቹን የምልክት አጠቃቀምና ዐረፍተ ነገር አሠራር በጥንቃቄ በመከታተል መዘገብና ለቀጣይ ትምህርቶች በግብአትነት መጠቀም*

## የክርክር አጠቃቀም

*መምህራን የክርክር ዓላማ ተማሪዎቹን ንቁ ተሳታፊ ለማድረግና የተማሯቸውን ምልክቶች፣ ዐረፍተ ነገሮችና የፊትና የአካል እንቅስቃሴዎች የእራሳቸውን ሐሳብ ለመግለጽ እንዲጠቀሙበት ለማበረታታት*

መሆኑን ተገንዝበው ዓላማው የሚሳካበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለባቸው።

ተማሪዎቹን በሁለት ቡድን ከፍሎ የክርክሩን ርእስ እና ሥርአት ካስረዱ በኋላ አስፈላጊውን እርምትና እርዳታ እያደረጉ ተማሪዎቹ ሐሳባቸውን በነጻ ማስረዳት የሚችሉባቸው ዕድሎችን ማመቻቸት

## የምልክቶች ትንተና

ሁሉም ምልክቶች  ከአምስት ትናንሽ ክፍሎች ወይም እሴቶች እንደሚሰሩ በማስረዳት ምልክቶች በዘፈቀደ እንደማይሰሩና ሥርአት እንዳላቸው ተማሪዎቹ እንዲገነዘቡ መርዳት

## ናሙና ሰዋስው

በአሁኑ ወቅት የኢምቋ ሰዋስው ስርአቶች በስርአቱ ተጠንተው ውጤቱም በመልክ በመልኩ ተለይቶ ባይዘገብም ስርአቱ በተናጋሪዎቹ ዘንድ የታወቀ ነው። በየምዕራፉ መጨረሻ የቀረቡት ናሙና ሰዋስዎች አራት ዓላማዎች አሏቸው፤

- ተማሪዎቹ የኢምቋ የራሱ የሆነ ሰዋሰው እንዳለው ግንዛቤ እንዲጨብጡ ለመርዳት፣
- ተማሪዎቹን የኢምቋ ሰዋስው ጋር ለማስተዋወቅ፣
- ተማሪዎቹ በአማርኛና በኢምቋ ሰዋስው መካከል ያለውን ልዩነት እንዲያዩ ለመርዳት፣
- ምንባቡን በኢምቋ ሊያነበብ የሚችልበትን መንገድ ለማሳያት፤ ወደ የኢምቋ ሰዋስው የተለወጡት ሁሉም የአማርኛ  ሰዋስው የተወሰዱት ከምንባቡ ውስጥ ነው። መምህሩ እነዚህን ምሳሌዎች መሠረት በማድረግ ምንባቡን በአጠቃላይ ወደ ኢምቋ ለመለወጥ ይችላል።

# ምዕራፍ አንድ
# የሥራ ፍቅር

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

* የሥራ አስፈላጊነትን በምክንያትና በውጤት አስደግፈው በኢምቋ ያስረዳሉ፡፡
* ከምንባቡ ውስጥ ዋናና ዝርዝር ሐሳቦችን ይለያሉ፡፡
* ከሥራ ጋር የተያያዙ ምልክቶችን በአግባቡ ይጠቀማሉ፡፡
* ከቁልፍ ምልክቶች ተጨማሪ ምልክቶችን ይመሠርታሉ፡፡
* ለምልክቶች ተመሳሳይና ተቃራኒ ይሰጣሉ፡፡
* የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮች ይሠራሉ፡፡
* የምልክቶችን ትናንሽ ክፍሎች ይተነትናሉ፡፡
* የኢምቋ እና የአማርኛ ሰዋስው ስርአቶችን ልዩነት ያስረዳሉ፡፡
* ሥርዓት ጠብቀው ይወያያሉ፡፡

**የሚያስፈልገው ክፍለ ጊዜ ብዛት፡** ዘጠኝ ክፍለ ጊዜያት

*መርጃ መሳሪያዎች*

- የኢምቋ መዝገብ ምልክት
- የአካባቢውን የሥራ ባህል የሚያሳዩ ሥዕሎች

*ርእሱን ማብራራት*

- ርእሱን ማስተዋወቅ፡ ሐሳቡ ግልጽ እስኪሆንላቸው ድረስ ማስረዳት፣
- የ‹‹ፍቅር›› ምልክት ከሥራ ጋር ሲሆን ኮስተር ካለ ፊት ጋር እንደሚሄድ ማስረዳት

ሥራ + ፍቅር = የሥራ ፍቅር

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### መልመጃ አንድ፡ ዕይታዊ ንባብ

*መምህር/ት፣*

*የዚህ መልመጃ ዓላማ የምዕራፉን ቁልፍ ምልክቶች ለማስተዋወቅ እንደሆነ ያስታውሱ፡፡*

- ሥዕሎቹን በጥንቃቄ አጥንተው መልስ በመስጠት እንዲሳተፍ ተማሪዎቹን ያበረታቷቸው
- የተማሪዎቹ መልስ እንደተማሪው አመለካከት ሊለያይ ይችላል፡፡ ትኩረቱ የምልክት አጠቃቀማቸው ላይ ይሁን፡፡
- ተማሪዎቹ መልስ በሚሰጡበት ግዜ የሚጠቀሙባቸውን ምልክቶች ወካይ ቃላት በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይጻፉ፡፡
- በውይይቱ መጨረሻ ላይ ከቁልፍ ምልክቶቹ ውስጥ ያልተጠቀሰ ካለ እርስዎ በዝርዝሩ ላይ ይጨመሩ፡፡
- ከተማሪዎቹ ጋር በመሆን ምልክቶቹን ከጣት ፊዳለቸው ጋር ይድገሙ፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ምንባብ

*መምህር/ት፣*

*ምንባቡን ከማንበብዎ በፊት የሚከተሉትን ያከናውኑ፤*

- ቀደም ብለው የተዘጋጁትን የምንባቡን ቁልፍ ምልክቶች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጽፎ አሠራራቸውን ማሳየት፣ ጽንሰ ሐሳባቸውን ማስረዳት፡፡ ዝርዝሩ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤
  - ሥራ
  - ፍቅር/መውደድ
  - ማድረግ
  - አባባል
  - ማንነት
  - ስኬታማ
  - አስተዋጽኦ
  - ታዋቂ
  - የበለጸጉ
  - ዜጋ
  - እርካታ
  - እምነት
  - ውጤታማ
  - መጣር
  - ማጥላላት
- ለቁልፍ ምልክቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት ምንባቡን ለተማሪዎቹ ማንበብ
- የምንባቡን ሐሳብ የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮችን በመጠቀም ማቅረብ
- ተማሪዎቹ ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች እንዲጠይቁ ማበረታታ
- ተማሪዎቹ ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ትምህርት ዝግጅት ምንባቡን በግላቸው አንበበው እንዲመጡ ማባረታታት

## መልመጃ አንድ

ጥያቄዎቹ ተማሪዎቹ በምንባቡ ውስጥ የተማሯቸውን ምልክቶች ለመለማመድና ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ምልክቶች አጠቃቀም ግንዛቤያቸውን ለማስፋትታስበው የተዘጋጁ ስለሆኑ በክፍል ውስጥ በኢምቀ እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

1. እያንዳንዱ ተማሪ ከምንባቡ አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ በክፍል ውስጥ በኢምቋ እንዲያቀርብ ያበረታቷቸው፡፡
2. ተማሪዎቹ የምንባቡን መልዕክት በራሳቸው አቀራረብ በክፍሉ ወስጥ በአጭሩ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡
3. በመጨረሻ እርስዎ በተማሪዎቹ አቀራረብ ውስጥ የታዩትን ክፍተቶች በማረም መልመጃውን ያጠናቁ፡፡

## መልመጃ ሁለት

### መልሶች

1. ሰውን ከሌሎች ፍጡራን የሚለየው ሥራው ነው፡፡
2. የበለጸጉ ሀገሮች የደረሱበት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ከረዷቸው ምክንያቶች አንዱ የዜጎቻቸው የሥራ ፍቅር ነው፡፡
3. ስቴቭ ጆብስን ለዕውቅና ያበቃው በሥራው ያስመዘገበው ስኬት ነው፡፡
4. አንድ ሰው የሚሠራውን ሥራ የሚወድ ከሆነ ሥራዬ ታላቅ ሥራ ነው የሚል እምነት ያድርበታል፡፡ ይህ እምነት ደግሞ በሥራው ውጤታማ የመሆን ዕድሉን ያሰፋዋል፡፡
5. ደከመኝ-ሰለቸኝ ሳይሉ በመሥራት፣ በጠዋት ወደ ሥራ በመሄድና እስኪመሽ በመሥራት፣ በሙሉ ልባቸውና በደስታ ሥራቸውን በማከናወን፣ ሥራቸውን ሊያበላሹባቸው ከሚችሉ ሰዎች ወይም ነገሮች በመራቅ፣ የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም በሥራቸው ውጤታማ ለመሆን በመጣር፣ ስለ ሥራቸው መልካምነት በመናገር፣ ሥራ የማይወዱትን በማጥላላትና ለሌሎች ሰዎች የሥራን ጥሩነት በመናገር ወዘተ

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## መልመጃ አንድ፡ የቡድን ስራ

መምህር/ት፡

ተማሪዎቹ በአካባቢያችው ሰዎች የሥራ ፍቅርን በሚገልጹባቸው መንገዶች ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ የውይይቱ ዋና ዓላማ ከሥራ ጋር የተያያዙ ምልክቶች አጠቃቀም መሆኑን አይዘንጉ፡፡ በውይይቱ መጨረሻ ላይ ተማሪዎቹ የተጠቀሙባቸውን አዳዲስ ምልክቶች ዝርዝር አዘጋጅተው ከተማሪዎቹ ጋር ይከልሱ፡፡

## መልመጃ ሁለት፡ ዐረፍተ ነገሮች ግንባታ

መምህር/ት፣

ዐረፍተ ነገሮች በተለያየ መንገድ ሊገነቡ እንደሚችሉ ለተማሪዎቹ በምሳሌዎች ያሳዩአቸው፡፡ ከዚያም ተማሪዎቹ የተሰጧቸውን ምልክቶች በተለያዩ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ በመጠቀም ልዩነት እንዲፈጥሩ ያበረታቷቸው፡፡

## መልመጃ ሦስት፡ የምልክቶች ተቃራኒ ማሳየት

የመልመጃው መልሶች የሚከተሉት ምልክቶች ናቸው

1. መጥላት
2. ውድቀት
3. መደህየት
4. መነቃቃት
5. ማሞገስ

## መልመጃ አራት፡ የምልክቶች ርባታ

የሚከተሉት ቃላት ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡ ናቸው፡፡ ተማሪዎቹ በቃላቱ ከተወከሉት ምልክቶች አዳዲስ ምልክቶችን በመፍጠር በክፍል ውስጥ እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡

ምሳሌ፡

ብልጽግና (ምልክት፡ ሀብት)

ባለጸጋ (ምልክት፡ ሀብታም)

መበልጸግ (ምልክት፡ ሀብታም + መሆን)

1. *ሥራ-ባለሥራ-መሥራት*
2. ፍቅር-አፍቃሪ-ማፍቀር
3. ማድረግ-አድራጊ-ማድረግ
4. ዕውቅና-ታዋቂ-መታወቅ
5. እድገት-ያደገ-ማደግ
6. እምነት-አማኝ-ማመን
7. ውጤት-ውጤታማ-ውጤታማ መሆን
8. ዕድል-ዕድለኛ-ዕድለኛ መሆን
9. መጣር-ታታሪ-ጥረት
10. ማጥላላት- ጠዪ-መጥላት

## ክፍለ ትምህርት አራት፡ የምልክቶች ትንተና

መምህር/ት፡-

ተማሪዎቹ ቀደም ባሉት ክፍሎች በተማሩት መሠረት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተማሯቸውን ዋና ዋና ምልክቶች ትናንሽ ክፍሎች ትንተና በክፍል ውስጥ እንዲያሳዩ ያበረታቷቸው፡፡ በተማሪዎቹ መጽሐፍ ውስጥ የተቀመጡትን ምልክቶች ቢጠቀሙ ይበረታታል፡፡

ምሳሌ፡

*ሥራ*



1. የእጅ ቅርጽ፡ የተጨበጠ እጅ
2. የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ፡ የተጨበጠው እጅ ላይ
3. የመዳፍ አቅጣጫ፡ ግራ-ቀኝ
4. የእጅ እንቅስቃሴ፡ ወደ ላይና ታች
5. በእጅ የማይገለጹ ክፍሎች፡ ኮስተር ያለ ፊት

## ክፍለ ትምህርት አምስት፡ ኢምቋ ሰዋስው ናሙናዎች

1. አማርኛ፡ ሰውን ሰው ያደረገው ሥራው ነው፡፡

   ኢምቋ፡ ሰው ሰው አደረገ ምን- ሥራ

2. አማርኛ፡ ሥራ ክቡር ነው፡፡

   ኢምቋ፡ ሥራ የተከበረ

3. አማርኛ፡ ሥራን መውደድ ስኬታማ ያደርጋል፡፡

   ኢምቋ፡ ሥራ ወደደ ስኬት ይቻላል

4. አማርኛ፡ ዜጎች ሥራ ሲወዱ ሀገር ትለማለች፡፡

   ኢምቋ፡ ዜጋ ሥራ ወደደ ሀገር ልማት መጣ

5. አማርኛ፡ ሀገራችን እንድታድግ ከፈለግን ሥራ መውደድ አለብን፡፡

   ኢምቋ፡ እኛ ሀገር መልማት ፈለገ-ሥራ መውደድ ግድ

## መልመጃ

መምህር/ት፡

የዚህ መልመጃ ዋንኛ ዓላማ ተማሪዎቹ የኢምቋ ትምህርትን ተምረው የጨረሱ እንዳይመስላቸው፣ ገና ወደ ፊት መማር የሚገባቸው ብዙ ትምህርት እንዳለ እንዲረዱና ለዚሁ እንዲነሳሱ ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎቹ መልመጃውን እንዲሞክሩ ከማበረታታት ባለፈ፣ ትክክለኛ መልስ እንዲሰጡ አያስገድዷቸው ፡፡ በማንኛውም ፈተና ውስጥም አያካቱት፡፡

ተማሪዎቹ የሚሰጧቸው መልሶች የሚከተሉትን ማጠቃለላቸውን ያረጋግጡ፤

1. የቃላት/የምልክቶች ቅደም ተከተል
2. በግሶች ላይ የግዜ ገላጮች አጠቃቀም

3. **የብዛት ገላጮች አጠቃቀም**
4. **የሀረጎች አዋቀቀር አጠቃቀም**
5. **የሐሳብ ቅደም ተከተል አጠቃቀም**
6. **የዐፍተ ነገር አጫራረስ አጠቃቀም**

# ምዕራፍ ሁለት

# ባህላዊ ቅርሶች

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

* ከባህላዊ ቅርሶች ጋር የተያያዙ ምልክቶቸን በአግባቡ ይጠቀማሉ፡፡
* በኢትዮጵያና በአካባቢያቸው ስለሚገኙ ባህላዊ ቅርሶች ያስረዳሉ፣ ያከብራሉ፣ ይንከባከባሉ፡፡
* ከቅርስ ጋር የተያያዙ ምልክቶችን በትክክል ይጠቀማሉ፡፡
* በአካባቢያቸው ያሉ ባህላዊ ልምዶችን ይገልጻሉ፡፡
* ከቁልፍ ምልክቶች አዳዲስ ምልክቶችን ይመሰርታሉ፡፡
* የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮች ይሠራሉ፡፡
* ለምልክቶች ተመሳሳይና ተቃራኒ ምልክቶች ይሰጣሉ፡፡
* በኢምቋ ግጥም የማንበቢያ ሥርዓቶችን በመጠቀም አጫጭር ግጥሞችን በዜማ መልክ በኢምቋ ያነባሉ፣ መልእክታቸውንም ያስረዳሉ፡፡
* የምልክቶችን ክፍሎች ይተነትናሉ፡፡
* በውይይት ማጠቃለያ ሐሳብ ላይ ይደርሳሉ፡፡
* ከኢምቋ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ስም ይለያሉ፡፡

የሚያስፈልገው ክፍለ ጊዜ ብዛት፡ አሥራ አንድ ክፍለ ጊዜያት

### መርጃ መሣሪያዎች

- የኢምቋ መዝገብ ምልክት
- ከተቻለ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ባህላዊ ቅርሶች ፎቶዎች ወይም ስዕሎች፡፡

### ርዕሱን ማብራራት

- ርዕሱን ማስተዋወቅ፡ ሐሳቡ ግልጽ እስኪሆንላቸው ድረስ ማስረዳት
- ባህል + ቅርስ + ነገሮች = ባህላዊ ቅርሶች

## ክፍለ ትምህርት አንድ፡ ዕይታዊ ንባብ

*የዚህ መልመጃ ዓላማ የምዕራፉን ቁልፍ ምልክቶች ለማስተዋወቅ እንደሆነ ያስታውሱ፡፡*

- ፎቶ ግራፎቹን በጥንቃቄ አጥንተው መልስ በመስጠት እንዲሳተፉ ተማሪዎቹን ያበረታቷቸው
- የተማሪዎቹ መልስ እንደተማሪው አመለካከት ሊለያይ ይችላል፡፡ ትኩረቱ የምልክት አጠቃቀማቸው ላይ ይሁን፡፡
- ተማሪዎቹ መልስ በሚሰጡበት ጊዜ የሚጠቀሙባቸውን ምልክቶች ወካይ ቃላት በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይጻፉ፡፡
- በውይይቱ መጨረሻ ላይ ከቁልፍ ምልክቶቹ ውስጥ ያልተጠቀሰ ካለ እርስዎ በዝርዝሩ ላይ ይጨመሩ፡፡
- ከተማሪዎቹ ጋር በመሆን ምልክቶቹን ከጣት ፊዳላቸው ጋር ይድገሙ፡፡

*ቅርሶቹን ባህላዊ ቅርሶች ተብለው በዓለም አቀፍ ደረጃ ለመታወቅ ካበቃቸው ምክንያቶች መካል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፤*

- ከተለመደው ለየት ያለ ገጽታቸው፣ አሠራራቸው፣ ወዘተ፣
- ጥንታዊነታቸው

♦ ውበታቸው ወይም መስህብነታቸው

♦ የያዙት መልዕክት ወይም ይዘታቸው

## ክፍለ ትምህርት ሁለት

*ምንባቡን ከማንበብዎ በፊት የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውኑ፤*

♦ ቀደም ብለው የተዘጋጁትን የምንባቡን ቁልፍ ምልክቶች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጽፎ አሠራራቸውን ማሳየት፤ ጽንሰ ሐሳባቸውንም ማስረዳት፡፡ ዝርዝሩ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤

- ባህላዊ
- ቅርስ
- ምድር
- ቁሳዊ
- የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት
- የሐረር ግንብ
- የአክሱም ሐውልቶች
- የአዋሽ ሸለቆ
- እደ ጥበብ
- ዜማ
- አርበኛ
- የተባበሩት መንግሥታት
- ኮሚሽን
- የሰሜን ተራሮች
- አፋር
- ሰነድ

♦ ከላይ የተቀመጡትን ምልክቶች ካሳዩ በኋላ፤ ለቁልፍ ምልክቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት ምንባቡን ለተማሪዎቹ ማንበብ

♦ የምንባቡን ሐሳብ የኢምቂ ዐረፍተ ነገሮችን በመጠቀም ማቅረብ

♦ ተማሪዎቹ ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች እንዲጠይቁ ማበረታታ

- ተማሪዎቹ ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ትምህርት ዝግጅት ምንባቡን በግላቸው አንበበው እንዲመጡ ማባረታታት

## መልመጃ አንድ

መምህር፤ የጥያቄዎቹ ተማሪዎቹ በምንባቡ ውስጥ የተማሯቸውን ምልክቶች ለመለማመድና ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ምልክቶች አጠቃቀም ግንዛቤያቸውን ለማስፋትታስበው የተዘጋጁ ስለሆኑ በክፍል ውስጥ በኢምቋ እንዲመልሱ ያድርጉ።

1. እያንዳንዱ ተማሪ ከምንባቡ ውስጥ አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ በክፍል ውስጥ በኢምቋ እንዲያቀርብ ያበረታቱ።
2. ተማሪዎቹ የምንባቡን መልዕክት በአጭሩ በራሳቸው አቀራረብ በክፍሉ ወስጥ አንዲያቀርቡ ያድርጉ።

## መልመጃ ሁለት፡ የመልመጃው መልሶች

1. ባህላዊ ቅርሶች ማለት አንድ ኅዝብ የፈጠራቸውና በክብር ጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ ያስተላለፋቸው ቁሳዊና ቁሳዊ ያልሆኑ የጋራ ሀብቶች።
2. በዩኔስኮ የተመዘገቡት የኢትዮጵያ ባህላዊ ቅርሶች የማይዳሰስው ወይም መንፈሳዊ ቅርሳችን የመስቀል ወይም የደመራ በዓል፣ በትግራይ ክልል የሚገኙት የአክሱም ሐውልቶች፣ በአማራ ክልል የሚገኙት፤ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስትያናትና የፋሲል ግንብ፣ በደቡብ ክልል የሚገኙት የኮንሶ የእርከን ስራ፣ የኦሞ ሸለቆ እና የጥያ ትክል ድንጋዮች፣ በሐረሪ ክልል የሚገኘው ሐረር ጀጎል ወይም የሐረር ግንብ፣ በአፋር ክልል የሚገኘው የአዋሽ ሸለቆ ናቸው።
3. ባህላዊ ቅርሶች በሁለት ዋና ዋና ክፈል ይከፈላሉ፤ ባህላዊና ተፈጥሮአዊ።
4. የኅዝቡን ወይም የሀገሩን ታሪክ፣ ባህል፣ ማንነት ወዘተ፣ ለመጪው ትውልድ ያስተዋውቃሉ፣ ጎብኚዎችን በመሳብ ለሀገሪቱና ለአካባቢው ኅዝብ ገቢ ያስገኛሉ፣ ለሀገርና ለሕዝብ መልካም ገጽታ ግንባታ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፣ አዲሱ ትውልድ የቀድሞውን ትውልድ እንዲያከብርና በግዜውም የሚያኮራ ቋሚ ተግባር እንዲያከናውን ያበረታታሉ።
5. ማጥናት፣ መንከባከብና በሰነድ የማስቀመጥ።

## ክፍለ ትምህርት ሦስት፡ የቡድን ሥራ

መመህር/ት፣

ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋፈል በአካባቢያቸው ከሚገኙ ቅርሶች ውስጥ ባህላዊ ቅርሶች ተብለው በዩኔስኮ ከተመዘገቡት ቅርሶች ጋር የሚመሳሰሉ እንዳሉ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ የውይይቱ ዋንኛ ዓላማ እርስ በእርስ በመማማር ተማሪዎቹን ግንዛቤያቸውን እንዲያሰፉ ለመርዳት እንዲሁም የተማሯቸውን ቁልፍ ምልክቶች በተግባር እንዲጠቀሙባቸው ለማበረታታት ነው፡፡

## ክፍለ ትምህርት አራት

### መልመጃ አንድ፡ ዐረፍተ ነገር ግንባታ

መምህር/ት፣

ተማሪዎቹ ምልክቶቹን በተለያዩ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ እንዲጠቀሙ ያበረታቷቸው፡፡ በተቻለ መጠን ተማሪዎቹ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተሰጡትን የኢምቋ ሰዋሰው ናሙናዎች ምሳሌ እንዲከተሉ ያበረታቷቸው፡፡

### መልመጃ ሁለት፡ የምልክቶች ተቃራኒ ምልክት መፈለግ

መልሶች

1. ዘመናዊ
2. ቅርስ
3. ሰው ሰራሽ
4. የቤት እንስሳት
5. ቁሳዊ ያልሆኑ

## መልመጃ ሦስት

መምህር/ት፡ ተማሪዎቹ የ‹‹ዊ›› ማሳያ በምልክቶቹ ላይ በመጨመር እንዲያሳዩ ያድርጉ

ምሳሌ፡

ባህል

ባህላዊ፡ (ምልክት፡ ባህል + የ ‹‹ዊ›› ማሳያ)

1. ቁስዊ
2. መንፈስዊ
3. ኢትዮጵያዊ
4. ዓለም አቀፍዊ
5. ሀገራዊ

## ክፍለ ትምህርት አምስት፡ የምልክቶች ትንተና

ተማሪዎቹ የምዕራፉን ቁልፍ ምልክቶች ትናንሽ ክፍሎች በክፍል ውስጥ እየተነተኑ እንዲያሳዩ ያበረታቷቸው፡፡

ምሳሌ፡

ቅርስ



1. የእጅ ቅርጽ፡ ቀ
2. የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ፡ የግራ እጅ መዳፍ

3. የመዳፍ አቅጣጫ፡ ወደ ላይ
4. የእጅ እንቅስቃሴ፡ ዝግዛግ
5. በእጅ የማይገለጹ ክፍሎች፡ ነጻ

## ክፍለ ትምህርት ስድስት፡ ግጥም ማንበብ

*ግጥም በኢምቋ በሚነበብት ጊዜ አንባቢዊ ሊከተላቸው የሚገቡ መንገዶች አሉ፡፡ እነዚህን መንገዶች መከተል መልዕክቱን ግልጽ ከማድረግ በተጨማሪ ለአነባበቡ ውበት ይሰጣል፡፡ ተማሪዎቹ የሚከተለውን የአነባበብ መመሪያ በክፍል ውስጥ እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡*

1. በየእያንዳንዱ መስመር መጨረሻ ላይ ለአንድ ሴኮንድ ያህል የመጨረሻውን ምልክት የእጅ ቅርጽ በአየር ላይ ያዝ አድርጎ ማቆየት፣
2. በስንኝ መጨረሻ ላይ የመጨረሻውን ምልክት የእጅ ቅርጽ በአየር ላይ በመስመሮች መካከል ካለው የግዜ ክፍተት ረዘም ላለ ግዜ ያዝ አድርጎ ማቆየት፣
3. የስንኞችን የመጀመሪያ ምልክት ዝግ ብሎ ማሳየት፣
4. የእጆችን እንቅስቃሴን እንደ ግጥሙ ስሜትና መልዕክት ዝግ ወይም ፈጠን ማድረግ፡፡

### መልመጃ አንድ

*የተሰጠውን ግጥም የኢምቋ ሥርዓቶችን በጠበቀ መንገድ በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ ልምምዱ ሲያበቃ ተማሪዎቹ የመረጡትን ግጥም በተማሩት መሠረት ተለማምደው እንዲመጡና በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡*

### መልመጃ ሁለት፡ መልሶች

1. የግጥሙ መልዕክት ዓይነስውራን ለሚመሩበት ነጭ ብትር ያላቸው ፍቅርና የሚሰጧትን ዋጋ በማሳየት ሌሎች ተመሳሳይ ዋጋ እንዲሰጧት ለማበረታታት ነው፡፡
2. ዋስትና፣ ከለላ፣ የዓይን ምትክ፣ የልብ ጋደኛ፣ ታማኝ ወዳጅ፣ መሃንዲስ ወዘተ
3. እጅግ ከፍተኛ፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሰባት፡ የኢምቋ ሰዋሰው ናሙናዎች

1. አማርኛ፡ ሀገራችን ከምትታወቅባቸው መልካም ገጽታዎች አንዱ ቅርሶቻችን ናቸው፡፡

   ኢምቋ፡ እኛ ሀገር ታወቀ አንድ ምክንያ ምን-ቅርስ

2. አማርኛ፡ ቅርሶች ተፈጥሮአዊና ባህላዊ ተብለው በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ፡፡

   ኢምቋ፡ ቅርስ ሁለት ዋና ዋና ክፍል አለ ምን-ምን- አንድ ተፍጥሮዊ፣ ሁለት ባህላዊ

3. አማርኛ፡ ኢትዮጵያ በዩኔስኮ የተመዘገቡ አስር ቅርሶች አላት፡፡

   ኢምቋ፡ ኢትዮጵያ ዩ-ኔ-ስ-ኮ መዘገብ ቅርስ ስንት- አስር

4. አማርኛ፡ ባህላዊ ቅርሶች ለአንድ ኅዝብ ወይም ሀገር የሚያስገኙት ጥቅሞች ብዙ ናቸው፡፡

   ኢምቋ፡ ቅርስ ባህል ለኅዝብ ጥቅም ብዙ ሰጠ

5. አማርኛ፡ ባህላዊ ቅርሶቻችንን መንከባከብ የሁላችንም ግዴታ ነው፡፡

   ኢምቋ፡ ሁሉም ቅርስ ባህል መንከባከብ ግድ

## መልመጃ አንድ

መምህር/ት፡

የዚህ መልመጃ ዋንኛ ዓላማ ተማሪዎቹ የኢምቋ ትምህርትን ተምረው የጨረሱ እንዳይመስላቸውን ገና ወደ ፊት ለመማር የሚገባቸው ብዙ ትምህርት እንዳለ እንዲረዱና ለዚሁ እንዲነሳሱ ለማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎቹ መልመጃውን እንዲሞክሩ ከማበረታታት ባለፈ ትክክለኛ መልስ እንዲሰጡ የግድ አይበሏቸው፡፡ በማንኛውም ፈተና ውስጥም አያካቱት፡፡

መልሶች

በናሙናዎቹ ውስጥ ያሉ ስሞች፤

ሀገር፣ ቅርስ፣ ኢትዮጵያ፣ ዩ-ኔ-ስ-ኮ፣ ኅዝብ

# ምዕራፍ ሦስት
# ሰብአዊ መብቶች

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

- ከመብት ጋር የተያያዙ ምልክቶችን በአግባቡ ይጠቀማሉ፡፡
- ስለሰብአዊ መብቶች ምንነትና ጥቅም ያስረዳሉ፡፡
- የመስማት የተሳናቸው መብቶች ተከበሩ የሚባለው ምን ሲሟላ እንደሆነ ያብራራሉ፡፡
- ተጋባዣ ተናጋሪ ማስተናገድ ይለማመዳሉ፣
- ከተለያዩ ምንጮች መረጃዎችን በማሰባሰብ በክፍል ውስጥ ማቅረብ ይለማመዳሉ፣
- በምልክቶች እርባታ ውስጥ የ‹‹አችን››ን አጠቃቀምና ትርጉም ያስረዳሉ፡፡
- የኢምቋ ሰዋስው ግንዛቤያቸውን ያሳድጋሉ፡፡
- አያያዦችን በዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ይጠቀማሉ፡፡
- ትረካ ያቀርባሉ፡፡
- ከቁልፍ ምልክቶች አዳዲስ ምልክቶችን ይመሠርታሉ፡፡
- የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮች ይሠራሉ፡፡
- ለምልክቶች ተመሳሳይና ተቃራኒ ምልክቶች ይሰጣሉ፡፡
- የምልክቶችን ክፍሎች ይተነትናሉ፡፡
- በውይይት ማጠቃለያ ሐሳብ ላይ ይደርሳሉ፡፡

የሚያስፈልገው ክፍለ ጊዜ ብዛት፡ ዘጠኝ ክፍለ ጊዜያት

መርጃ መሣሪያዎች

- የኢምቋ መዝገብ ምልክት
- ከተለያዩ ምንጮች የተሰባሰቡ ከርእሱ ጋር የተያያዙ ፎቶዎች

ርእሱን ማብራራት

- ርእሱን ማስተዋወቅ፡ ሐሳቡ ግልጽ እስኪሆንላቸው ድረስ ማስረዳት
- ሰው + የ‹‹ዊ›› ማሳያ + መብት= ሰበአዊ መብቶች

## ክፍለ ትምህርት አንድ፡ ዕይታዊ ንባብ

*የዚህ መልመጃ ዓላማ የምዕራፉን ቁልፍ ምልክቶች ለማስተዋወቅ እንደሆነ ያስታውሱ፡፡*

- ፎቶግራፎቹን በጥንቃቄ አጥንተው መልስ በመስጠት እንዲሳተፍ ተማሪዎቹን ያበረታቷቸው
- የተማሪዎቹ መልስ እንደተማሪው አመለካከት ሊለያይ ይችላል፡፡ ትኩረቱ የምልክት አጠቃቀማቸው ላይ ይሁን፡፡
- ተማሪዎቹ መልስ በሚሰጡበት ጊዜ የሚጠቀሙባቸውን ምልክቶች ወካይ ቃላት በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይጻፉ፡፡
- በውይይቱ መጨረሻ ላይ ከቁልፍ ምልክቶቹ ውስጥ ያልተጠቀሰ ካለ እርስዎ በዝርዝሩ ላይ ይጨመሩ፡፡
- ከተማሪዎቹ ጋር በመሆን ምልክቶቹን ከጣት ፊደላቸው ጋር ይድገሙ፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ምንባብ

*ምንባቡን ከማንበብዎ በፊት የሚከተሉትን ያከናውኑ፤*

- ቀደም ብለው የተዘጋጁትን የምንባቡን ቁልፍ ምልክቶች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጽፎ አሠራራቸውን ማሳየት፣ ጽንሰ ሐሳባቸውን ማስረዳት፡፡ ዝርዝሩ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤

- ሰብአዊ
- መብት
- ተቋማት
- መርሕ
- ማርቀቅ/አርቅቆ
- በማኀበራቸው
- ጥረት
- ፌዴሬሽን
- ጥምር
- ተደራሽነት
- ማስተርጎም
- ዕውቅና
- መረጃ
- ትኩረት

*ከላይ የተቀመጡትን ምልክቶች ካሳዩ በኋላ፤*

- ለቁልፍ ምልክቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት ምንባቡን ለተማሪዎቹ ማንበብ
- የምንባቡን ሐሳብ የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮችን በመጠቀም ማቅረብ
- ተማሪዎቹ ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች እንዲጠይቁ ማበረታታት
- ተማሪዎቹ ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ትምህርት ዝግጅት ምንባቡን በግላቸው አንበበው እንዲመጡ ማባረታታት

## መልመጃ አንድ

ጥያቄዎቹ ተማሪዎቹ በምንባቡ ውስጥ የተማሯቸውን ምልክቶች ለመለማመድና ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ምልክቶች አጠቃቀም ግንዛቤያቸውን ለማስፋትታስበው የተዘጋጁ ስለሆኑ በክፍል ውስጥ በኢምቀ እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

1. እያንዳንዱ ተማሪ ከምንባቡ ውስጥ አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ በክፍል ውስጥ በኢምቋ

እንዲያቀርብ ያበረታቱ፡፡

2. ተማሪዎቹ የምንባቡን መልዕክት በአጭሩ በራሳቸው አቀራረብ በክፍሉ ወስጥ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

## መልመጃ ሁለት፡ የመልመጃው መልሶች

1. ሰብአዊ መብቶች ሁሉም ሰዎች ሰው በመሆናቸው ብቻ የተሰጣቸው መብቶች ናቸው፡፡
2. አራት ነገሮች መሟላት አለባቸው፡፡ እነሱም፤፤ የምልክት ቋንቋ፣ በጥምር ቋንቋ ላይ ያተኮረ ትምህርት፣ ተደራሽነትና የትርጉም አገልግሎት ማግኘት፡፡
3. ለምልክት ቋንቋ እንደ አንድ የሀገሪቱ ቋንቋ ዕውቅና መስጠት፣ መስማት የተሳናቸውም በምልክት ቋንቋቸው የመጠቀም መብታቸውን ማክበር፣ ማንኛውንም መረጃ በምልክት ቋንቋ ማግኘትና በምልክት ቋንቋ መማርን ወዘተ፣ ያጠቃልላል፡፡
4. የጥምር ቋንቋ ትምህርት አቀራረብ ማለት የሁሉም ትምህርቶች የማስተማሪያ ቋንቋ የምልክት ቋንቋ ሆኖ በተመሳሳይ ጊዜም ልጆቹ የማኅበረሰባቸውን ወይም የሀገራቸውን ቋንቋ የመጻፍና የማንበብ ብቃት እንዲኖራቸው ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ማስተማር ማለት ነው፡፡
5. ሁሉም መረጃዎች ተደራሽ መሆን አለባቸው፡፡ ሕጋዊ ሰነዶችን ጨምሮ ለኅዝቡ ተብለው የተዘጋጁ መረጃዎች በሙሉ በምልክት ቋንቋ መተርጎም አለባቸው፡፡ የዕለቱ ዋና ዋና ዜናዎችና ልዩ ፕሮግራሞች በምልክት ቋንቋ መቀረብ አለባቸው፡፡
6. የራሳቸውን የምልክት ቋንቋ አስተርጋሚ በመጠቀም መስማት የተሳናቸው እንድ ማንኛውም ተገልጋይ አገልግሎታቸውን በእኩልነት ማግኘት የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለባቸው፡፡

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## መልመጃ አንድ፡ ዐረፍተነገር ግንባታ

መምህር/ት፡ ተማሪዎቹ ምልክቶቹን በተለያዩ ዐረፍተነገሮች ውስጥ በመጠቀም የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮች በመሥራት በክፍል ውስጥ እንዲያሳዩ ያበረታቷቸው፡፡

## መልመጃ ሁለት፡ ባዶ ቦታ መሙላት

የመልመጃዎቹ መልሶች

1. ሰዎች
2. የዓለም መስማት የተሳናቸው ፌዴሬሽን
3. ዕውቅና
4. በጥምር ቋንቋ
5. በግላቸውናበማኅበራቸው

## መልመጃ ሦስት፡ የምልክቶች ርባታ

ምሳሌ፡

በግል

በግላችን ፡ (ምልክት፡ ግል + አችን)

የመልመጃ መልሶች

1. በማኅበራችን
2. በፌድሬሽናችን
3. በሀገራችን
4. በዓለማችን
5. በትምህርተ ቤታችን

## ክፍለ ትምህርት አራት፡ ተጋባዥ ተናጋሪ ማስተናገድ

መምህር/ት፡

አንድ የመስማት የተሳናቸው ማሕበረሰብ መሪ በመጋበዝመስማት ስለተሳናቸው ዜጎች ሰበአዊ መብቶች በክፍል ውስጥ ንግግር እንዲያደርጉ ያደርጉ፡፡ ተማሪዎቹም የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ተገቢውን ሥልጠና ይስጧቸው፡፡ ከንግግሩ በኂላ ተማሪዎቹን ወክሎ ለእንግዳው ምስጋና የሚያቀርብ ተወካይ መምረጥ፣

1. ተጋባዥ እንግዳው ወደ ክፍል ከመምጣታቸው በፊት የጥያቄ አጠያየቅ እንዲሁም የምስጋና ንግግር በሚደረግበት መንገድ ላይ ተወያይቶ መወሰን፣
2. ተጋባዥ እንግዳው ንግግር በሚያደርጉበት ጊዜ አጫጭር ማስታወሻ እንዴት እንደሚያዝ፣
3. ከተጋባዥ እንግዳው የኢምቋ አጠቃቀም ምን ለመማር መሞከር እንዳለባቸው፣
4. የምስጋና ንግግር በተወካይ በኩል እንዴት እንደሚቀርብ፡፡

## መልመጃ አንድ፡ የቡድን ሥራ

ከንግግሩ በኋላ ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋፈል የሚከተሉትን እንዲያከናውኑና ቀጥሎ እንደተለመደው የቡድን ሥራ ውጤታቸውን በክፍል ውስጥ በኢምቋ እንዲያቀርቡ ያድርጉ።

1. በንግግሩ ወቅት የያዙትን የግል ማስታወሻ በማስተያየት በንግግሩ ላይ መወያየት፣
2. ከንግግሩ የተማሯቸውን ትምህርቶች ዝርዝር ማዘጋጀት፣
3. ከተጋባኙ እንግዳው የተማሯቸውን አዳዲስ ምልክቶች ዝርዝር ማዘጋጀት።

## ክፍለ ትምህርት አምስት፡ የምልክቶች ትንተና

ምሳሌ፡



መብት

1. የእጅ ቅርጽ፡ ግማሽ ክብ- የተጨበጠ እጅ
2. የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ፡ የግራ እጅ መዳፍ ላይ
3. የመዳፍ አቅጣጫ፡ ወደ ግራ
4. የእጅ እንቅስቃሴ፡ እየተዘጋ ወደ ፊት
5. በእጅ የማይገለጹ ክፍሎች፡ ኮስታራ ፊት

## ክፍለ ትምህርት ስድስት፡ የኢምቋ ሰዋስው ናሙናዎች

1. አማርኛ፡ ሰብዓዊ መብቶች ሁሉም ሰዎች ሰው በመሆናቸው ብቻ የተሰጣቸው

መብቶች ናቸው፡፡

ኢምቋ፡ መብት ሰው ምን - ሁሉም ሰው ተሰጠ እኩል መብት- ልዩ ልዩ የለም መብት፡፡

2. አማርኛ፡ የዓለም መስማት የተሳናቸው ፌዴሬሽን የመስማት የተሳቸውን ሰበአዊ መብቶች ለማስከበር አራት መሠረታዊ ነገሮች መሟላት አለባቸው ብሎ ያምናል፡፡

ኢምቋ፡ መስማት የተሳናቸው ፌዴሬሽን ዓለም አለ ምን-የመስማት የተሳናቸው መብት ክብር መጀመሪያ አራት መስፈርት መሟላት ግድ፡፡

3. አማርኛ፡ መስማት የተሳናቸው በጥምር ቋንቋ ትምህርት አቀራረብ በመማር ጥራት ያለው ትምህርት የማግኘት መብታቸው መከበር አለበት፡፡

ኢምቋ፡ መስማት መሳን አንድ በራስ ምልክት ቋንቋ ሁለት ንግግር በሁለት ቋንቋ መማር ጥራት ትምህርት ማግኘት መብት ክብር አስፋጊ፡፡

4. አማርኛ፡ መስማት የተሳናቸው ነጻ እና በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ

ለማድረግ እንዲችሉ ሁሉም መረጃዎች ተደራሽ መሆን አለባቸው፡፡

ኢምቋ፡ መስማት መሳን ግራ ቀኝ መመዘን ቀጥሎ መወሰን መቻል አስፈላጊ ምን መረጃ ማግኘት መርዳት፡፡

5. አማርኛ፡ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት

አገልግሎታቸውን ለመስማት የተሳናቸው ተደራሽ ማድረግ አለባቸው፡፡

ኢምቋ፡ መንግሰት- መንግሰት ያለሆነ ሁለቱም የራስ የራሰ አገልግሎት መሰማት መሳን ማግኘት ማድረግ ግዴታ፡፡

## መልመጃ፡ አያያገኘች

አያያዦች ቃልን ከቃል/ምልክትን ከምልክት፣ ሐረግን ከሐረግ እንዲሁም ዐረፍተ ነገርን ከዐረፍተ ነገር ጋር በማያያዝ ትርጉምን ግልጽ የሚያደርጉ ቃላት/ምልክቶች ናቸው፡፡

በኢምቋ የሚገኙ አያያዦች ምሳሌ፡ እና፣ ስለዚህ፣ ወይም ወዘተ፣ ናቸው፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

- ከሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ጋር የተያያዙ ምልክቶችን በአግባቡ ይጠቀማሉ፡፡
- የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ምንነት፣ መንስኤዎችና ውጤቱን ያስረዳሉ፡፡
- የምንባብን ዋና ዋና እና ዝርዝር ሐሳቦችን ይለያሉ፡፡
- ለምልክቶች ቀጥተኛ ትርጉም ይሰጣሉ፡፡
- ከቁልፍ ምልክቶች አዳዲስ ምልክቶች ይፈጥራሉ፣፡
- አስተዋጽኦ ነድፈው አጭር ንግግር ያደርጋሉ፡፡
- ከዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ግሶችን ይለያሉ፡፡
- ከተለያዩ ምንጮች መረጃዎችን በማሰባሰብ በክፍል ውስጥ ማቅረብ ይለማመዳሉ፡፡
- የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮች ይሠራሉ፡፡
- ለምልክቶች ፍቺና ተቃራኒ ምልክቶች ይሰጣሉ፡፡
- የምልክቶችን ክፍሎች ይተነትናሉ፡፡
- በውይይት ማጠቃለያ ሐሳብ ላይ ይደርሳሉ፡፡

የሚያስፈልገው ክፍለ ጊዜ ብዛት፡ ዘጠኝ ክፍለ ጊዜያት

መርጃ መሣሪያዎች

- የኢምቋ መዝገብ ምልክት
- ከተለያዩ ምንጮች የተሰባሰቡ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ የሚያሳዩ ፎቶዎች

ርእሱን ማብራራት

- ርእሱን ማስተዋወቅ፡ ሐሳቡ ግልጽ እስኪሆንላቸው ድረስ ማስረዳት
- ህጻን + ጉልበት + መበዝበዝ = የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ

## ክፍለ ትምህርት አንድ፡ ዕይታዊ ንባብ

*የዚህ መልመጃ ዓላማ የምዕራፉን ቁልፍ ምልክቶች ለማስተዋወቅ እንደሆነ ያስታውሱ፡፡*

- ሥዕሉን በጥንቃቄ አጥንተው መልስ በመስጠት እንዲሳተፍ ተማሪዎቹን ያበረታቷቸው
- የተማሪዎቹ መልስ እንደተማሪው አመለካከት ሊለያይ ይችላል፡፡ ትኩረቱ የምልክት አጠቃቀማቸው ላይ ይሁን፡፡
- ተማሪዎቹ መልስ በሚሰጡበት ግዜ የሚጠቀሙባቸውን ምልክቶች ወካይ ቃላት በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይጻፉ፡፡
- በውይይቱ መጨረሻ ላይ ከቁልፍ ምልክቶቹ ውስጥ ያልተጠቀሰ ካለ እርስዎ በዝርዝሩ ላይ ይጨመሩ፡፡
- ከተማሪዎቹ ጋር በመሆን ምልክቶቹን ከጣት ፊደላቸው ጋር ይድገሙ፡

## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ምንባብ

*ምንባቡን ከማንበብዎ በፊት የሚከተሉትን ያከናውኑ፤*

- ቀደም ብለው የተዘጋጁትን የምንባቡን ቁልፍ ምልክቶች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጽፎ አሠራራቸውን ማሳየት፣ ጽንስ ሐሳባቸውን ማስረዳት፡፡ ዝርዝሩ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤
  - ጉልበት
  - ብዝበዛ

- ክፋት
- ኃላቀርነት
- ቁርኝት
- መጥፎ
- ማስወገድ
- ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር
- መደበኛ ያልሆኑ ሥራዎች ዘርፍ
- ማዕድን
- ግንባት/ኮንስትራክሽን
- አደገኛ
- የጤና ጉዳት
- መከላከል
- ሱስ
- ማኅበራዊ ቀውስ

*ከላይ የተቀመጡትን ምልክቶች ካሳዩ በኋላ፤*

- ለቁልፍ ምልክቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት ምንባቡን ለተማሪዎቹ ማንበብ
- የምንባቡን ሐሳብ የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮችን በመጠቀም ማቅረብ
- ተማሪዎቹ ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች እንዲጠይቁ ማበረታታት
- ተማሪዎቹ ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ትምህርት ዝግጅት ምንባቡን በግላቸው አንብበው እንዲመጡ ማበረታታት

## መልመጃ አንድ፡ ዕይታዊ ንባብ

የመልመጃው መልሶች

1. አስከፊ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ከድህነትና ከኋላ ቀርነት ጋር  የተቆራኘ ነው፡፡
2. የዓለም ሥራ ድርጅት እ.ኤ.አ. 2010 ያወጣው ዓመታዊ ሪፖርት በዓለማችን 215 ሚሊዮን

የሚገመቱ ሕፃናት በጉልበት ብዝበዛ ውስጥ ተሰማርተው አስከፊ ሕይወት እየመሩ እንደሚገኙ ያስረዳል፡፡ ከነዚህ መካከል 115 ሚሊዮን የሚሆኑት ለደህንነታቸውና ለጤንነታቸው እጅግ አደገኛና ጠንቀኛ በሆኑ ሥራዎች ላይ ተሰማርተው፣ የትምህርት ዕድል ተከልክለው እና ሰብአዊ ክብራቸውን ተነፍገው በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንደሚገኙ ያመለክታል፡፡

3. አስከፊ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ በስፋት የሚታይባቸው የዓለማችን ክፍሎች እስያ እና አፍሪካ ናቸው፡፡ በላቲን አሜሪካና በምሥራቅ አውሮፖ ሀገሮችም ክስተቱ የሚታይ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

4. በዓለም ሥራ ድርጅት ሪፖርት መሠረት ለሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ መስፋፋት ዋነኛ ምክንያቶች የድህነት ሁኔታ፣ ጦርነትና መፈናቀል፣ የኤችአይቪ/ኤድስ፣ ወረርሽኝ ፣ የተሳሳተ የማኅበረሰብ አመለካከት፣ በቂ ሕግና የሕግ ጥበቃ ሥርዓት ያለመኖርና የሕገ ወጥ ሕፃናት ዝውውር መበራከት ናቸው፡፡

5. ሕፃናት በብዛት ከተሰማሩባቸውና ለአስከፊ ብዝበዛ ከተጋለጡባቸው ዋና ዋና የሥራ ዘርፎች መካከል፤ መደበኛ ያልሆኑ የሥራ ዘርፎች፣ በቤት ውስጥ የሚሰሩ ሥራዎች፣ ፋብሪካዎችና የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣ እርሻ ልማቶች፣ የማዕድን ቁፋሮ ሥራዎች፣ የኮንስትራክሽን ሥራዎች፣ አገልግሎት ሰጪዎች፣ የሆቴሌና የቱሪዝም ሥራዎች ይጠቀሳሉ፡፡

## መልመጃ ሁለት፡ የምልክቶች ፍቺና ተቃራኒ ማሳየት

የሚከተሉት ቃላት ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡ ናቸው፡፡ በቃላቱ የተወከሉትን ምልክቶች ፍቺና ተቃራኒ ምልክቶች በክፍል ውስጥ በኢምቂ እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡

1. ብዝበዛ
   *ፍቺ፡* የአንድን ሰው ንብረት፣ እውቀት ጉልበት ወዘተ ተገቢ ዋጋ ሳይከፍሉ መወሰድ፡፡
   ተቃራኒ፡ ልገሳ/መለገስ
2. ኋላቀርነት
   *ፍቺ፡* ከጊዜው ጋር የሚመጣጠን የእድገት ደረጃ ላይ አለመድረስ፡፡
   *ተቃራኒ፡* እድገት/ ዘመናዊነት
3. ቁርኝት
   *ፍቺ፡* ትስስር፣ ግንኙነት
   *ተቃራኒ፡* ልዩነት
4. ጠንቀኛ
   *ፍቺ፡* ጎጂ አደገኛ
   *ተቃራኒ፡* ጠቃሚ
5. ሕገወጥ
   *ፍቺ፡* ሕግ ያልተከተለ
   *ተቃራኒ፡* ሕጋዊ

## መልመጃ ሦስት፡ የምልክቶች ርባታ

መልመጃ መልሶች

ምሳሌ፡

ብዝበዛ ድርጊት

ተበዝባዥ ድርጊቲ የተከናወነበተ ሰው

በዝባዥ ድርጊቱን ያደረገው ሰው

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | ጉዳት | ተጊጂ | ጎጂ |
| 2. | ጥቃት | ተጠቂ | አጥቂ |
| 3. | እርዳታ | ተረጂ | ረጂ |
| 4. | ጥቅም | ተጠቃሚ | ጠቃሚ |
| 5. | ሞት | ማች | ገዳይ |

## ክፍለ ትምህርት ሦስት፡ የምልክቶች ትንተና

ምሳሌ፡



ብዝበዛ

1. የእጅ ቅርጽ፡ ከአመልካች ጣት በስተቀር ሁሉም የተጨበጠ እጅ
2. የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ፡ ብብት አካባቢ
3. የመዳፍ አቅጣጫ፡ ወደ ውስጥ
4. የእጅ እንቅስቃሴ፡ ከግራ ወደ ቀኝ እንደ መምጠጥ

5. በእጅ የማይገለጹ ክፍሎች፡ የመምጠጥ ሁኔታ

## መልመጃ አንድ፡ ንግግር

መምህር/ት፡

የዚህ ክፍል ዓላማ ተማሪዎቹ ስለ ጉልበት ብዝበዛ የተዛባ አመለካከት ጨብጠው ቤተሰብን ለመርዳት እንዳያንገራግሩ ወይም ቤተሰብ እርዳታ ስለጠየቃቸው እንደ ጉልበት ብዝበዛ እንዳያዩ ለመርዳት ነው፡፡ ስለዚህ ቤተሰብን በሥራ ማገዝና ከአቅም በላይ መሥራት በሚለው ርእስ ላይ አጭር የኢምቋ ንግግር አዘጋጅተው በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ በማድረግ ተማሪዎቹ ትክክለኛ ግንዛቤ መጨበጣቸውን ያረጋግጡ፡፡

ማስታወሻ፡ አስተዋጽኦ የአንድ ሰፊ ንግግር ዋና ዋና እና አጫጭር ነጥቦች ናቸው፡፡

## ክፍለ ትምህርት አራት፡ የኢምቋ ናሙና ሰዋስው

1. አማርኛ፡ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ከድህነትና ከኋላ ቀርነት ጋር ቁርኝት አለው፡፡

   ኢምቋ፡ ሕፃናት ጉልበት መበዝበዝ፣ ድህነት፣ ኋላ ቀርነት- ሦስት የተያያዘ

2. አማርኛ፡ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ በስፋት ከሚታይባቸው ሀገሮች አንዷ አፍሪካ ነች፡፡

   ኢምቋ፡ የሕፃናት ጉልበት መበዝበዝብዙ ብዙ ሀገር አለ አንድ ማ-በስፋት አፍሪካ፡፡

3. አማርኛ፡ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ በላቲን አሜሪካና በምሥራቅ አውሮፖ ሀገሮችም አለ፡፡

   ኢምቋ፡ የሕፃናት ጉልበት መበዝበዝ አፍሪካ ብቻ- አይደለም ደቡብ አሜሪካ በምሥራቅ አውሮፖ ተመሳሳይ አለ፡፡

4. አማርኛ፡ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ሕገወጥ ተግባር ነው፡፡

   ኢምቋ፡ የሕፃናት ጉልበት መበዝበዝ ሕገ መስበር ስህተት ተግባር፡፡

5. አማርኛ፡ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛን በጋራ መታገልና ማስቆም አለብን፡፡

   ኢምቋ፡ አብሮ መሥራት፣ መታል የሕፃናት ጉልበት መበዝበዝ ማስቆም አስፈላጊ፡፡

## መልመጃ

መምህር/ት፡ ይህን ክፍል የሚመለከተው የኢምቋ ጥናት ገና በሂደት ላይ ነው፡፡ የዚህ መልመጃ ዋንኛ ዓላማ ተማሪዎቹ የኢምቋ ትምህርትን ተምረው የጨረሱ እንዳይመስላቸውን ገና ወደ ፊት ለመማር የሚገባቸው ብዙ ትምህርት እንዳለ እንዲረዱና ለዚሁ እንዲነሳሱ ለማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎቹ መልመጃውን እንዲሞክሩ ከማበረታታት ባለፈ ትክክለኛ መልስ እንዲሰጡ የግድ አይበሏቸው፡፡ በማንኛውም ፈተና ውስጥም አያካቱት፡፡

# ምዕራፍ አምስት
# የታዋቂ ሴቶች የሕይወት ታሪክ

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

* ስለ ታዋቂ ሴቶች የሕይወት ታሪክ በተለያየ መንገድ ከተረዱ በኋላ፣ የራሳቸውንና የሌሎችን የሕይወት ታሪክ በኢምቁ ይተርካሉ፡፡
* የአንድን የኢምቁ ትረካ መልዕክትያወጣሉ፡፡
* የኢምቁ ግሶች የርባታ ቅጥያዎችን በተግባር ያሳያሉ፡፡
* ቀደም ብለው የተማሩትን የክርክር ስርአቶች ያዳብራሉ፡፡
* የምልክቶች ትንተናና የኢምቁ ሰዋስው ችሎታቸውን ያሳድጋሉ፡፡
* ከዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ግሶችን ትለያላችሁ፡፡
* የምንባቡን ዋና ዋና እና ዝርዝር ሀሳቦችን ይለያሉ፣
* ለምልክቶች ቀጥተኛ ትርጉም ይሰጣሉ፣
* ከቁልፍ ምልክቶች አዳዲስ ምልክቶች ይፈጥራሉ፡፡
* የኢምቁ ሰዋስው ግንዛቤያቸውን ያሳድጋሉ፡፡
* የኢምቁ ዐረፍተ ነገሮች ይሠራሉ፡፡
* ለምልክቶች ተመሳሳይና ተቃራኒ ምልክቶች ይሰጣሉ፡፡
* የምልክቶችን ክፍሎች ይተነትናሉ፡፡
* በውይይት ማጠቃለያ ሐሳብ ላይ ይደርሳሉ፡፡

የሚያስፈልገው ክፍለ ጊዜ ብዛት፡ስምንት ክፍለ ጊዜያት

## መርጃ መሣሪያዎች

- የኢምቋ መዝገብ ምልክት
- ከተለያዩ ምንጮች የተሰባሰቡ ተማሪዎቹ የሚያውቃቸው የታዋቂ ሴቶች ፎቶዎች

## ርእሱን ማብራራት

- ርእሱን ማስተዋወቅ፡ ሐሳቡ ግልጽ እስኪሆንላቸው ድረስ ማስረዳት
- ሴቶች + ታዋቂ + ታሪክ + ግል = የታዋቂ ሴቶች ግለ ታሪክ

## ክፍለ ትምህርት አንድ፡ ዕይታዊ ንባብ

*የዚህ መልመጃ ዓላማ የምዕራፉን ቁልፍ ምልክቶች ለማስተዋወቅ እንደሆነ ያስታውሱ፡፡*

- ሥዕሉን በጥንቃቄ አጥንተው መልስ በመስጠት እንዲሳተፍ ተማሪዎቹን ያበረታቷቸው፡፡
- የተማሪዎቹ መልስ እንደተማሪው አመለካከት ሊለያይ ይችላል፡፡ ትኩረቱ የምልክት አጠቃቀማቸው ላይ ይሁን፡፡
- ተማሪዎቹ መልስ በሚሰጡበት ግዜ የሚጠቀሙባቸውን ምልክቶች ወካይ ቃላት በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይጻፉ፡፡
- በውይይቱ መጨረሻ ላይ ከቁልፍ ምልክቶቹ ውስጥ ያልተጠቀሰ ካለ እርስዎ በዝርዝሩ ላይ ይጨመሩ፡፡
- ከተማሪዎቹ ጋር በመሆን ምልክቶቹን ከጣት ፊደላቸው ጋር ይድገሙ፡፡ በምታዩት ምስል መሠረት የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ምን እንደሆነ አስረዱ፡፡

*ምንባቡን ከማንበብዎ በፊት የሚከተሉትን ያከናውኑ፤*

- ቀደም ብለው የተዘጋጁትን የምንባቡን ቁልፍ ምልክቶች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጽፎ አሠራራቸውን ማሳየት፤ ጽንሰ ሐሳባቸውን ማስረዳት፡፡ ዝርዝሩ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤
  - የሕይወት ታሪክ
  - ሥራ ዘርፍ

- ዕውቅና ማግኘት
- ሳይንቲስት
- ምርምር
- ጥናት
- ዕጽዋት
- አዝዕርት
- ባክቴሪያ
- ተዋህስያን
- የእንስሳት መኖ
- ማዕከል
- ዳይሬክተር
- ሹመት
- አካዳሚ

*ከላይ የተቀመጡትን ምልክቶች ካሳዩ በኋላ፤*

- ለቁልፍ ምልክቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት ምንባቡን ለተማሪዎቹ ማንበብ
- የምንባቡን ሐሳብ የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮችን በመጠቀም ማቅረብ
- ተማሪዎቹ ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች እንዲጠይቁ ማበረታታት
- ተማሪዎቹ ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ትምህርት ዝግጅት ምንባቡን በግላቸው አንብበው እንዲመጡ ማበረታታት

## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ምንባብ

### መልመጃ አንድ

የመልመጃው መልሶች

1. የዶክተር ሰገነት የምርምር ዘርፍ የግብርና ሳይንስ ነው፡፡
2. ለዶክተር ሰገነት ከፍተኛ ዕውቅና ያስገኘላቸው ምርምራቸው ባራኬሪያ በሚባል ባክቴሪያ ላይ

ያደረጉት ምርምር ነው፡፡

3. ለዶክተር ሰገነት በአሁኑ ወቅት ኬንያ ውስጥ የሚገኝ አንድ ትልቅ ዓለም አቀፍ የግብርና ምርምር ማዕከል ዋና ዳይሬክተር ናቸው፡፡

4. ዶክተር ሰገነት የሚመሩት የምርምር ማዕከል በአፍሪካ ውስጥ ጥናቶችን በማካሄድ የሃብት እጥረት ያለባቸውን የአህጉሩን የገጠርና የከተማ ማኅበረሰቦች ይደግፋል፡፡

5. ለዶክተር ሰገነት የተሰጡት ሽልማቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፤ ሲአይኤቲ ከሚባል ዓለም አቀፍ ተቋም ለታዋቂ ተመራማሪዎች የሚበረከተውን ሽልማት፣ ከቻይና የወዳጅነት ሽልማት፣ የዓለም የሳይንስ አካዳሚ ሽልማት፣ የዩኔስኮ ሽልማት፡፡

## መልመጃ ሁለት

መምህር/ት፡ ጥያቄዎቹን ለተማሪዎቹ በተለያየ ፍጥነት በኢምቋ በማንበብ ኢምቋ አይቶ የመረዳት (በዓይን የመስማት) ችሎታቸውን ለማዳበር ይሞክሩ፡፡

1. ሀሰት
2. ሀሰት
3. እውነት
4. እውነት
5. ሀሰት
6. ሀሰት
7. ሀሰት
8. እውነት
9. እውነት
10. ሀሰት

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## መልመጃ አንድ፡ ትረካ

መምህር/ት፡

ተማሪዎቹ በአካባቢያችው የሚታወቁ አንዲት ሴት ታሪክ ጠይቀው ያገኙትን መረጃ የዶክተር ስገነት ታሪክ በተተረከበት መንገድ በማስተካከል በክፍል ውስጥ እንዲተርኩ ያድርጉ፡፡ ባለታሪኳ የግድ በጣም ታዋቂ መሆን የለባትም፡፡ ልጆቹ ስለእናታቸው መተረክም ይችላሉ፡፡ ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ መባል የሌለበት ነገር እንዳይሉ እንዲሁም ትረካው መያዝ ያለበትን ነጥብ ማካተቱን ለማረጋገጥ በመጀመሪያ ተማሪዎቹ የትረካቸውን ዋና ዋና ነጥቦች በጽሑፍ አዘጋጅተው እንዲያሳዩ ማድረግ ይመከራል፡፡ በተጨማሪም የሚከተሉትን ያስታውሱ፤

- የትረካ ዓላማ ተማሪዎቹ የተረዱትን በራሳቸው መንገድ መልሰው በማስረዳት የመረዳታቸውን መጠን እንዲያሳዩና እግረ መንገዳቸውንም የንግግር ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ መርዳት ነው፡፡ መምህራን ትረካውን ይህ ክሂል ሊዳብር በሚችልበት መንገድ ማመቻቸት አለባቸው፡፡
- በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት ነጥቦች በተማሪዎቹ ትረካ ውስጥ መካተታቸውን መከታተልና አስፈላጊውን እርማትና ድጋፎች ማድረግ፡፡
- የተማሪዎቹን የምልክት አጠቃቀምና ዐረፍተ ነገር አሠራር በጥንቃቄ በመከታተል መዘገብና ለቀጣይ ትምህርቶች በግብአትነት መጠቀም፡፡

## መልመጃ ሁለት፡ የምልክቶች እርባታ

የመልመጃው መልሶች

ምሳሌ፡

| | |
|---|---|
| ምርምር | ድርጊት |
| ተመራማሪ | ድርጊቱን ያደረገው ሰው |

1. ሳይንስ ሳይንቲስት
2. ጥናት አጥኚ
3. ማወቅ አዋቂ
4. ሽልማት ተሸላሚ
5. ሹመት ሿሚ

## መልመጃ ሦስት፡ ለሽልማት እጩ ማቅረብ

1. ተማሪዎቹ በአካባቢያቸው ወይም በሀገር አቀፍ ደረጃ ለአረያነት ብቁ የሆኑ አንዲት ሴት በእጩነት እንዲመርጡ ያድርጉ፣
2. የመረጧቸው እጩ ሴት በምን ነጥብ ዙሪያ እንደመረጡ በዝርዝር እንዲጽፉ ያድርጉ፣
3. ያዘጋጁትን ዝርዝር በመጠቀም የመረጧቸው ሴት ለአረያነት ብቁ ስለመሆናቸው የክፍል ጓደኞቻቸውን ለማሳመን በክፍል ውስጥ ንግግር እንዲያደርጉ ያድርጉ፤
4. ተማሪዎቹ በሚያቀርቧቸው ገላጻዎች አሳማኝነት መሠረት ንግግሩን እየገመገሙ ውጤት ይስጡ፡፡

*በተጨማሪም የሚከተሉትን ያስታውሱ፤*

የክርክር ዓላማ ተማሪዎቹን ንቁ ተሳታፊ ለማድረግና የተማሯቸውን ምልክቶች፣ ዐረፍተ ነገሮችና የፊትና የአካል እንቅስቃሴዎች የራሳቸውን ሐሳብ ለመግለጽ እንዲጠቀሙበት ለማበረታታት መሆኑን ተገንዝበው ዓላማው የሚሳካበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይጠበቅብዎታል፡፡

የክርክሩን ርእስ እና ሥርአት ካስረዱ በኋላ አስፈላጊውን እርምትና እርዳታ እያደረጉ ተማሪዎቹ ሐሳባቸውን በነጻ ማስረዳት የሚችሉባቸው ዕድሎችን ማመቻቸት አለበዎት፡፡

## ክፍለ ትምህርት አራት፡ የምልክቶች ትንተና

ቀደም ባሉት ክፍሎች በተማሩት መሠረት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተማሯቸውን  ዋና ዋና ምልክቶች ትናንሽ ክፍሎች ትንተና በክፍል ውስጥ እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡

ምሳሌ፡

*ታሪክ*



1. የእጅ ቅርጽ፡ ተ
2. የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ፡ ከደረት ፊት ለፊት
3. የመዳፍ አቅጣጫ፡ ወደ ውጭ
4. የእጅ እንቅስቃሴ፡ ወደ ላይና ታች
5. በእጅ የማይገለጹ ክፍሎች፡ ነጻ

## ክፍለ ትምህርት አምስት፡ የኢምቋ ናሙና ሰዋስው

1. አማርኛ፡ በተለያዩ መስኮች ራሳቸውንና ሀገራችንን የሚያኮሩ ተግባራት ያከናወኑ ብዙ ኢትዮጵያውያን ሴቶች አሉ፡፡

   ኢምቋ፡ ኢትዮጵያ ሴት ተለያያ ሥራ ራስ በደንብ መታወቅ ሀገር ኩራት ስሜት መቻል ብዙ አለ፡፡

2. አማርኛ፡ በተለያዩ መስኮች አኩሪ ተግባራት በማከናወን ዕውቅና ካተረፉ ሴት ኢትዮጵያውን አንዷ ዶክተር ሰገነት ቀለሙ ይባላሉ፡፡

   ኢምቋ፡ ኢትዮጵያ ሴት ተለያያ ሥራ እራስ በደንብ መታወቅ ሀገር ኩራት ስሜት መቻል ብዙ አለ- አንድ ማን- ሰገነት ዶክተር፡፡

3. አማርኛ፡ ዶክተር ሰገነት ቀለሙ ሳይንቲስት ናቸው፡፡

   ኢምቋ፡ ሰገነት ዶክተር ሥራ ምን-ሳይንስ መመራመር፡፡

4. አማርኛ፡ ዶክተር ሰገነት የሚመራመሩበት መስክ የግብርና ሳይንስ ነው፡፡

ኢምቋ፡ ሰገነት ዶክተር ምርምር አይነት ምን እርሻ ሳይንስ።

5. አማርኛ፡ ሳይንቲስቷ ባደረጓቸው የተለያዩ ምርምሮችና ባገኛቸው ውጤቶች ብዙ ሽልማቶችን ተቀብለዋል።

ኢምቋ፡ ሰገነት ዶክተር ምርምር ብዙ አደረገ ውጤት አገኘ ብዙ ተመሳሳይ ሽልማት ብዙ ማግኘት።

## መልመጃ

የኢምቋ ግሶች የርባታ ቅጥያዎች

ድርጊቱ ወይም ክንውኑ የተደረገበትን ግዜ ለማሳየት ግሶች ላይ ለውጥ ይደረጋል። ይህም የግሶች ርባት ይባላል።

መልሶች

- እንደ አማርኛ ግሶች ላይ ቅጥያ አይደረግም
- ከግሶቹ በፊት ወይም በኋላ ሌላ ምልክት በመጠቀም ግሱ አላፊ፣ አሁን ወይም የወደፊት አመልካች መሆኑን ማሳየት ይቻላል።

*መምህር/ት የሚከተሉትን ምሳሌዎች በጥንቃቄ አንብበው ተማሪዎቹ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ያድርጉ፤*

በክንውን ላይ ያለ ድርጊትን ለማሳየት ግሱ ይደጋገማል

ምሳሌ፡

አማርኛ፡ አበበ ቁርሱን እየበላ ነው።

ኢምቋ፡ አበበ ቁርስ መብላት መብላት

ያለፈ ድርጊትን ለማሳየት ከግሱ በኋላ የመጨረስ ምልክት ይከተላል።

ምሳሌ፡

አማርኛ፡ አበበ ቁርሱን በልቷል።

ኢምቋ፡ አበበ ቁርስ መብላት መጨረስ

ወደፊት የሚከናወኑ ተግባራትን ላማሳየት ከግሱ በፊት ወይም በኋላ የገና ምልክት ይጨመራል

ምሳሌ፡

አማርኛ፡ አበበ ቁርሱን አልበላም፡፡

ኢምቋ፡ አበበ ቁርስ መብላት ገና ወይም

አማርኛ፡ አበበ ቁርሱን ይበላል፡፡

ኢምቋ፡ አበበ ቁርስ መብላት በኋላ

# ምዕራፍ ስድስት
# በረሐማነት

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

* በረሃማነት የሚያስከትለውን ችግር ያስረዳሉ፡፡
* በረሐማነትን ለመከላከል የሚያስችሉ የመፍተሔ ሐሳቦች ያቀርባሉ፡፡
* የቡድን ሥራ ክሂላቸውን ይገነባሉ፡፡
* የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮች በመሥራትና ያልተማሉ ዓረፍተ ነገሮችን በማማላት የዐረፍተ ነገር ግንባታ ችሎታቸውን ያሳድጋሉ፡፡
* ከዐረፍተ ነገር ውስጥ ባለቤት ያወጣሉ፡፡
* ካርታ ያነባሉ፡፡
* ውይይት ሲካሄድ ቃለ-ጉባኤ ይይዛሉ፡፡
* ምልክቶች ይተነትናሉ፡፡
* የኢምቋ ሰዋስው ችሎታቸውን ያሳድጋሉ፡፡

የሚያስፈልገው ክፍለ ጊዜ ብዛት፡ አስር ክፍለ ጊዜያት

**መርጃ መሣሪያዎች**

- የኢምቋ መዝገብ ምልክት
- መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ላይ ያተኮሩ የአፍሪካና የኢትዮጵያ ካርታዎች

**ርእሱን ማብራራት**

- ርእሱን ማስተዋወቅ፡ ሐሳቡ ግልጽ እስኪሆንላቸው ድረስ ማስረዳት
- ደረቅ + ቦታ + የ‹‹ነት›› ምልክት = በረሃማነት

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### መልመጃ አንድ፡ ዕይታዊ ንባብ

*የዚህ መልመጃ ዓላማ የምዕራፉን ቁልፍ ምልክቶች ለማስተዋወቅ እንደሆነ ያስታውሱ፡፡*

- ሥዕሉን በጥንቃቄ አጥንተው መልስ በመስጠት እንዲሳተፍ ተማሪዎቹን ያበረታቷቸው፡፡
- የተማሪዎቹ መልስ እንደ ተማሪው አመለካከት ሊለያይ ይችላል፡፡ ትኩረቱ የምልክት አጠቃቀማቸው ላይ ይሁን፡፡
- ተማሪዎቹ መልስ በሚሰጡበት ጊዜ የሚጠቀሙባቸውን ምልክቶች ወካይ ቃላት በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይጻፉ፡፡
- በውይይቱ መጨረሻ ላይ ከቁልፍ ምልክቶቹ ውስጥ ያልተጠቀሰ ካለ እርስዎ በዝርዝሩ ላይ ይጨመሩ፡፡
- ከተማሪዎቹ ጋር በመሆን ምልክቶቹን ከጣት ፊደላቸው ጋር ይድገሙ፡፡

### መልመጃ ሁለት፡ ካርታ ማንበብ

መምህር/ት፡ ወደ ክፍል ያመጡትን የአፍሪካ እና የኢትዮጵያ ካርታ ሁሉም ተማሪዎች በግልጽ ሊያዩት በሚችሉበት ቦታ በመስቀል ተማሪዎቹ ካርታውን እያነበቡ በረሃማ አካባቢዎች የሚባሉትን ለይተው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡ በጣት በመጠቆም ሳይሆን ሐረጎችንና ዐረፍተ ነገሮችን በመጠቀም መልስ

እንዲሰጡ ያበረታቱ፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ምንባብ

*ምንባቡን ከማንበብዎ በፊት የሚከተሉትን ያከናውኑ፤*

- ቀደም ብለው የተዘጋጁትን የምንባቡን ቁልፍ ምልክቶች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጽፎ አሠራራቸውን ማሳየት፣ ጽንሰ ሐሳባቸውን ማስረዳት፡፡ ዝርዝሩ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤
  - ሥራ
  - ፍቅር/መውደድ
  - ማድረግ
  - አባባል
  - ማንነት
  - ስኬታማ
  - አስተዋጽኦ
  - ታዋቂ
  - የበለጸጉ
  - ዜጋ
  - እርካታ
  - እምነት
  - ውጤታማ
  - መጣር
  - ማጥላላት

*ከላይ የተቀመጡትን ምልክቶች ካሳዩ በኋላ፤*

- ለቁልፍ ምልክቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት ምንባቡን ለተማሪዎቹ ማንበብ፤
- የምንባቡን ሐሳብ የኢምቂ ዐረፍተ ነገሮችን በመጠቀም ማቅረብ፤
- ተማሪዎቹ ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች እንዲጠይቁ ማበረታታት፤

- ተማሪዎቹ ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ትምህርት ዝግጅት ምንባቡን በግላቸው አንብበው እንዲመጡ ማበረታታት፡፡

## መልመጃ አንድ

ጥያቄዎቹ ተማሪዎቹ በምንባቡ ውስጥ የተማሯቸውን ምልክቶች ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ምልክቶች አጠቃቀም ግንዛቤያቸውን ለማስፋት ታስበው የተዘጋጁ ስለሆኑ በክፍል ውስጥ በኢምቋ እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

1. እያንዳንዱ ተማሪ ከምንባቡ ውስጥ አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ በክፍል ውስጥ በኢምቋ እንዲያቀርብ ያድርጉ፡፡
2. ተማሪዎቹ የምንባቡን መልዕክት በአጭሩ በራሳቸው አቀራረብ በክፍሉ ወስጥ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

## መልመጃ ሁለት

የመልመጃው መልሶች

1. በምንባቡ መሠረት በረሐማነት የደን መመናመንን ተከትሎ የሚመጣ የአካባቢ አየር መዛባት፣ ሙቀት መጨመር፣ የዝናብ እጥረት፣ ወዘተ፣ ነው፡፡
2. በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ አሳሳቢ እየሆኑ ከመጡት ጉዳዮች አንዱ የአየር ንብረት መለወጥ ሲሆን፣ መንስኤዎቹ ደግሞ የደን መመናመንና በረሐማነት ናቸው፡፡
3. በምንባቡ ውስጥ በተጠቀሰው ዜማ መሠረት የቀድሞው የሀገራችን ሁኔታ በአረንጓዴ ዛፎችና ዕጸዋት የተሸፈነ ለምለምና ለዓይን እጅግ ደስ የሚል ነበር፡፡
4. መንግሥት በረሐማነትን ለመከላከል እቅድ ነድፎ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን እቅዱ የማያቋርጥ የችግኝ ተከላ፣ የእርከን ግንባታ፣ እንዲሁም ኅዝቡን በደን መራቆት ምክንያት ስለሚከሰቱ ፈርጀ ብዙ አደጋዎች ግንዛቤ ማስጨበጥን፣ ወዘተ፣ ያጠቃልላል፡፡
5. በረሐማነትን ለመከላከል ወጣቱ ትውልድ በረሐማነትን መከላከል የሕልውና ጉዳይ እንደሆነ የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር የበኩሉን መወጣትና በችግኝ ተካላና እንክብካቤ በንቃት መሳተፍ ይጠበቅበታል፡፡

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## መልመጃ አንድ፡ የቡድን ሥራ

- መምህር በመጀመሪያ ስለቃለ ጉባኤ አያያዝ ገለጻ ያድርጉላቸው፣
- ቀጥሎ እንደተለመደው ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋፈል ከቡድናቸው አንድ ውይይቱን የሚመራ ተማሪና አንድ ቃለ ጉባኤ ያዥ እንዲመርጡ ያድርጉ፣
- ቀደም ባሉት ክፍሎች በተማሩት የውይይት ሥርዓት መሠረት በረሐማነት በሚያስከትለው ችግርና መወሰድ በሚገባው መፍትሄ ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ፣
- በውይይቱ ወቅት እየተዘዋወሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉ እንዲሁም ተማሪዎቹ የሚጠቀሙባቸውን አዳዲስ ምልክቶች ይመዝግቡ፣
- በውይይቱ መጨረሻ ላይ ቃለ ጉባኤ የያዙት ተማሪዎች የቡድናቸውን ውይይት ቃለ ጉባኤ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርብ ያድርጉ፣
- የሁሉም ቡድኖች ቃለ ጉባኤ ከቀረበ በኋላ በቃለ ጉባኤ አያያዝና አቀራረብ በኩል የተመለከቱትን ክፍተት የሚሞላ ትምህርት ይስጡ፣
- አዳዲስ ምልክቶችን ማካፈልንም አይዘንጉ።

## መልመጃ ሁለት፡ ዐረፍተ ነገር ግንባታ

በመጀመሪያ ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡትን ቃላት ምልክቶች ያሳዩ። የምልክቶቹን ጽንሰ ሐሳብም ያስረዱ። ቀጥሎ ተማሪዎቹ ምልክቶቹን በተለያዩ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ እየተጠቀሙ እንዲያሳዩ ያበረታቷቸው።

1. በረሐማነት
2. አረንጓዴ ልማት
3. ድርቅ
4. ደን
5. ሕልውና

## መልመጃ ሦስት፡ የምልክቶች ተቃራኒ ማሳየት

የመልመጃው መልሶች

1. መትከል የ መንቀል ምልክት
2. መመናመን የ መብዛት ምልክት
3. አይን ይማርኩ የ የሚያስጠሉ ምልክት
4. መራቆት የ መሙላት ምልክት
5. ህልውና የ አለመኖር ምልክት

## መልመጃ አራት፡ ጅምር ዐረፍተ ነገሮችን ማጠናቀቅ

የመልመጃው መልሶች

ምሳሌ፡

በበረሐማት ሲስፋፋ _________________ እጥረት ይከተላል።

መልስ፡ የዝናብ

1. የአየር ንብረት
2. በረሐማነትና የደን መመናመንን
3. የደን መመናመንን
4. ሀገራችን ኢትዮጵያ
5. በለምለምነቷ

## ክፍለ ትምህርት አራት

ቀደም ባሉት ክፍሎች በተማሩት መሠረት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተማሯቸውን ዋና ዋና ምልክቶች ትናንሽ ክፍሎች ትንተና በክፍል ውስጥ እንዲያሳዩ ያድርጉ።

ምሳሌ፡

በረሐ



1. የእጅ ቅርጽ፡ የተቆለመመ አመልካች ጣት
2. የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ፡ አገጭ
3. የመዳፍ አቅጣጫ፡ ወደ ውስጥ
4. የእጅ እንቅስቃሴ፡ ከግራ ወደ ቀኝ
5. በእጅ የማይገለጹ ክፍሎች፡ ጭፍግግ/ድርቅ ያለ ፊት

## ክፍለ ትምህርት አምስት፡ የኢምቋ ሰዋስው ናሙናዎች

ቀደም ባሉት ምዕራፎች ባደረጉት መሠረት ከዚህ በታች የቀረቡትን የኢምቋ ሰዋስው ናሙናዎች ለተማሪዎቹ ያብራሩ

1. አማርኛ፡ በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ አሳሳቢ እየሆኑ ከመጡት ጉዳዮች አንዱ የአየር ንብረት መለወጥ ነው፡፡

   ኢምቋ፡ አሁን ግዜ ዓለም ሁሉ ስጋት ስጋት ፈጠረ አንድ ምክንያት ምን- አየር ጠባይ ለወጥ ለወጥ፡፡

2. አማርኛ፡ ለአየር ንብርት መለወጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ ካሉት መካከል የደን መመናመንና በረሐማነት በስፋት ይጠቀሳሉ፡፡

   ኢምቋ፡ አየር ጠባይ ልውጥ ልውጥ ምክንያት ብዙ ብዙ- ዋና ዋና ምን- ዛፍ ዛፍ መቀነስ መቀነስ ቀጥሎ በረሐ መሆን ሰፋ-ሰፋ፡፡

3. አማርኛ፡ በረሐማነት የደን መመናመንን ተከትሎ የሚመጣ በመሆኑ ሁለቱ ችግሮች እርስ በእርስ የተያያዙ ናቸው፡፡

   ኢምቋ፡ ዛፉ ዛፍ መቀነስ መቀነስ መቀጠል መምጣት ምን በረሐ መሆን- ሁለት ሁለት

ተያያዘ፡፡

4. አማርኛ፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ በበረሐማነትን እየተጠቁ ካሉት ሀገሮች አንዷ ነች፡፡

ኢ.ምቋ፡ ዓለም በረሐ መሆን ሀገር ብዙ አንድ ማ- ሀገር የእኛ ኢትዮጵያ፡፡

5. አማርኛ፡ “እምዬ ኢትዮጵያ፣ ለምለሚቱ ሀገሬ፤ በጣም ደስ ይለኛል፣ ከአንቺ መፈጠሬ…!”

ኢ.ምቋ፡ እናት ኢትዮጵያ ለምለም ሀገር የኔ ፤እኔ ደስ ደስ ስሜት ምክንያት እኔ መወለድ አንቺ ፡፡

## መልመጃ፡ የዐረፍተ ነገር ባለቤት

ባለቤት ማለት አንድ ዐረፍተ ነገር የሚናገርለት ወይም ዐረፍተ ነገሩ ስለእሱ የሚያወራለት አንድ በስም ወይም በተውላጠ ስም የተወከለ አካል ማለት ነው፡፡ የዐረፍተ ነገር ባለቤት ሰው፣ ዕቃ ወይም ነገር ሊሆን ይቻላል፡፡

ይህን መሠረት በማድረግ ከላይ የተሰጡት የኢ.ምቋ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ የዐረፍተ ነገሩን ባለቤት ለይተው እንዲያሳዩ ያበረታቷቸው፡፡

# ምዕራፍ ሰባት
# መከባበር

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኂላ፡

* ስለመከባበር ምንነትና ማኀበራዊ ፋይዳ በተገቢው የኢምቋ አጠቃቀም ይገልጻሉ፡፡
* መረጃ ለማግኘት በኢምቋ ጥያቄዎች ይጠይቃሉ፡፡
* በአካባቢያቸው ሰዎች መከባርን በምን መልክ እንደሚያሳዩ በኢምቋ ያስረዳሉ፡፡
* የአክብሮች መግለጫ ምልክቶች ከነተቃራኒያቸው በኢምቋ ያሳያሉ፡፡
* በትምህርት ቤትና በክፍል ውስጥ መከባበርን ለማስፋፋት በግላቸው ማድረግ የሚችሏቸውን አስተዋጽኦዎች ለክፍል ጓደኞቻቸው ያካፍላሉ፡፡
* የራሳቸውን ዐረፍተ ነገሮች በኢምቋ ይመሠርታሉ፤ የተሰጧቸውንም የተጓደሉ ዐረፍተ ነገሮችን ያሟላሉ፡፡
* ምልክቶች ይተነትናሉ፡፡
* የኢምቋ ሰዋስው ችሎታቸውን ያሳድጋሉ፡፡

የሚያስፈልገው ክፍለ ጊዜ ብዛት፡ ዘጠኝ ክፍለ ጊዜያት

*መርጃ መሣሪያዎች*

· የኢምቋ መዝገብ ምልክት

· የሀገራችንን እና የአካባቢውን የመከባበር ባህል የሚሳዩ ሥዕሎች፣ ፎቶዎች፣ ወዘተ

ርእሱን ማብራራት

· ርእሱን ማስተዋወቅ፡ ሐሳቡ ግልጽ እስኪሆንላቸው ድረስ ማስረዳት

· እኔ + ክብር + አንተ + አንተ + እኔ + ክብር = መከባበር

እኔ + ክብር + አንተ- የሚገለጸው የክብርን ምልክት ከውስጥ ወደ ውጭ በመሥራት እንጂ የ ‹‹እኔ ›› እና የ‹‹አንተ›› ምልክቶችን ማከል አያስፈልግም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔት አንተ + እኔ + ክብር - የሚገለለጸው የክብርን ምልክት የከውጭ ወደ ውስጥ በመሥራት አንጂ የ‹‹አንተ ›› እና የ‹‹ እኔ›› ምልክቶች መሥራት አያስፈልግም፡፡

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### መልመጃ አንድ፡ ዕይታዊ ንባብ

*የዚህ መልመጃ ዓላማ የምዕራፉን ቁልፍ ምልክቶች ለማስተዋወቅ እንደሆነ ያስታውሱ፡፡*

- ሥዕሉን በጥንቃቄ አጥንተው መልስ በመሰጠት እንዲሳተፉ ተማሪዎቹን ያበረታቷቸው፡፡
- የተማሪዎቹ መልስ እንደ ተማሪው አመለካከት ሊለያይ ይችላል፡፡ ትኩረቱ የምልክት አጠቃቀማቸው ላይ ይሁን፡፡
- ተማሪዎቹ መልስ በሚሰጡበት ጊዜ የሚጠቀሙባቸውን ምልክቶች ወካይ ቃላት በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይጻፉ፡፡
- በውይይቱ መጨረሻ ላይ ከቁልፍ ምልክቶቹ ውስጥ ያልተጠቀሰ ካለ እርስዎ በዝርዝሩ ላይ ይጨመሩ፡፡
- ከተማሪዎቹ ጋር በመሆን ምልክቶቹን ከጣት ፊደላቸው ጋር ይድገሙ፡

## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ምንባብ

*ምንባቡን ከማንበብዎ በፊት የሚከተሉትን ያከናውኑ፤*

- ♦ ቀደም ብለው የተዘጋጁትን የምንባቡን ቁልፍ ምልክቶች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጽፎ አሠራራቸውን ማሳየት፣ ጽንሰ ሐሳባቸውን ማስረዳት፡፡ ዝርዝሩ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤
  - መከባበር
  - መለካምነት
  - መግለጫ
  - ጤናማ
  - ደስተኛ
  - ስኬታማ
  - ማኅበረሰብ
  - አስተዋጽኦ
  - ግለሰቦች
  - ብሔረሰቦች

*ከላይ የተቀመጡትን ምልክቶች ካሳዩ በኋላ፤*

- ♦ ለቁልፍ ምልክቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት ምንባቡን ለተማሪዎቹ ማንበብ
- ♦ የምንባቡን ሐሳብ የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮችን በመጠቀም ማቅረብ
- ♦ ተማሪዎቹ ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች እንዲጠይቁ ማበረታታት
- ♦ ተማሪዎቹ ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ትምህርት ዝግጅት ምንባቡን በግላቸው አንብበው እንዲመጡ ማበረታታት

### መልመጃ አንድ

ጥያቄዎቹ ተማሪዎቹ በምንባቡ ውስጥ የተማሯቸውን ምልክቶች ለመለማመድና ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ምልክቶች አጠቃቀም ግንዛቤያቸውን ለማስፋት ታስበው የተዘጋጁ ስለሆኑ በክፍል ውስጥ በኢምቋ እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

1. እያንዳንዱ ተማሪ ከምንባቡ ውስጥ አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ በክፍል ውስጥ በኢምቋ እንዲያቀርብ ያድርጉ፡፡
2. ተማሪዎቹ የምንባቡን መልዕክት በአጭሩ በራሳቸው አቀራረብ በክፍሉ ወስጥ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

## መልመጃ ሁለት

የመልመጃው መልሶች

1. ለመከባበር ልዩ ስፍራ የሰጡና እንደ  የመለካምነት መግለጫ የሚያዩ ምሳሌዎች፤ ጎዝቦች፣ ሀገሮች፣ ባህሎች፣ ሃይማኖቶች
2. በቤተሰብ ውስጥ መከባበር ሲኖር ቤተሰቡ ጤናማ፣ ደስተኛና ስኬታማ ቤተሰብ  ይሆናል፡፡
3. ግጭት ‹‹እኔ›› ያልኩት ብቻ ይሰማ፣ ይደረግ፣ ይሁን፣ ወዘተ፣ የሚል እብሪተኛ ስሜት ውጤት ነው፡፡ ይህ ስሜት ደግሞ መከባበር ባለመኖሩ የሚመጣ ስሜት ነው፡፡
4. መከባበር በሀገራችን ያስገኘውን ጥቅሞች ብዙ ናቸው፤ በመካከላችን ያለው የባህል፣ የሃይማኖት፣ የቋንቋ፣ የቀለም፣ ወዘተ፣ ልዩነት እንቅፋት ሳይሆንብን በአንድነት ከሦስት ሺ ዓመታት በላይ አብረን ለመኖር ችለናል፡፡ በመካከላችን የተፈጠሩ ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ችለናል፡ ፡ የጋራ ሀገራዊ ራዕይ ይዘን ለስኬታማነቱ በጋራ ለመሥራትና ሀገራችን ዛሬ ለምትገኝበት የእድገት ደረጃ ላይ ለማድረስ ችለናል፡፡
5. ልዩነቶችን በውይይት በመፍታት አብሮ በሰላም መኖር፣ የሌላውን መብት ማክበር፣ ግጭት እንዳይፈጠር መጠንቀቅ ወዘተ፡፡

## መልመጃ ሦስት

የመልመጃው መልሶች

1. መከባበር
2. መልካም ሁኔታ
3. ጤናማ፣ ደስተኛና ስኬታማ
4. ለስኬታማነት
5. ከሦስት ሺ

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## መልመጃ አንድ፡ የቡድን ሥራ

ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋፈል አለመከባበር በሚያስከትለው ችግርና መወሰድ በሚገባው መፍተሔ ላይ እንዲወያዩና የውይይታቸውን ውጤት በተወካያቸው በኩል ለክፍል ጓደኞቻችሁ እንዲያስረዱ ያድርጉ፡፡ በውይይቱ ወቅት እስካሁን የተማሯቸውን የውይይት ስርአቶች ተግባራዊ ማድረጋቸውን እንዲሁም ምልክቶችን በትክክል እየተጠቀሙ መሆኑን ያረጋግጡ፡፡

## መልመጃ ሁለት፡ ዐረፍተ ነገሮች ግንባታ

እንደተለመደው በመጀመሪያ ምልክቶቹን ወክለው የተቀመጡትን ቃላት ምልክቶች ያሳዩ፡፡ የምልክቶቹን ጽንሰ ሐሳብም ያስረዱ፡፡ ቀጥሎ ተማሪዎቹ ምልክቶቹን በተለያዩ የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮች እየተጠቀሙ እንዲያሳዩ ያበረታቷቸው፡፡

1. መከባበር
2. መለካምነት
3. መግለጫ
4. ጤናማ
5. ደስተኛ
6. ስኬታማ
7. ማኅበረሰብ
8. አስተዋጽኦ
9. ግለሰቦች
10. ብሔሰረሰቦች

## መልመጃ ሦስት፡ የምልክቶች ተቃራኒ ማሳየት

የመልመጃው መልሶች

ምሳሌ፡ መከባበር

ትርጉም እርስ በእርስ አክብሮት መሰጣጠት

ተቃራኒ መናናቅ

1. መለካምነት

   ትርጉም-መልካም መሆን

   ተቃራኒ- መጥፎነት

2. ደስተኛ

   ትርጉም- በደስታ መሞላት

   ተቃራኒ- ኃዘንተኛ

3. ስኬት

   ትርጉም- ውጤታማ መሆን

   ተቃራኒ- ውድቀት

4. ግጭት

   ትርጉም- ጥል

   ተቃራኒ-ፍቅር

5. እጦት

   ትርጉም- እጥረት ወይም አለመኖር

   ተቃራኒ- መኖርወይም መትረፍረፍ

## መልመጃ አምስት፡ የምልክቶች ርባታ

የመልመጃው መልሶች

ምሳሌ፡

ደስታ ደስተኝነት

1. የ ስኬታማነት ምልክት
2. የ መልካምነት ምልክት
3. የ ጤናማነት ምልክት

4. የ እብሪተኝነት ምልክት
5. የ ጥሩነት ምልክት

## ክፍለ ትምህርት አራት፡ የምልቶች ትንተና

መከባበር



1. የእጅ ቅርጽ፡ የተጣበቁ የሌባና የመሃል ጣቶች
2. የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ፡ ግንባር
3. የመዳፍ አቅጣጫ፡ ትይዩ
4. የእጅ እንቅስቃሴ፡ ከላይ ወደ ታች
5. በእጅ የማይገለጹ ክፍሎች፡ በአክብሮት ጎንበስ ማለት

## ክፍለ ትምህርት አምስት፡ የኢምቋ ናሙና ሰዋስው

ከዚህ በታች የቀረቡትን የኢምቋ ሰዋስው ናሙናዎች በጥንቃቄ አጥንታችሁ ከናሙናዎቹ ቀጥሎ የተሰጠውን መልመጃ ስሩ

1. አማርኛ፡ መከባበር የመልካምነት መግለጫ ነው፡፡

   ኢምቋ፡ እኔ አንተ ክብር- አንተ እኔ ክብር መግለጫ ምን- መልካም መሆን፡፡

2. አማርኛ፡ መከባበር ከሚደነቁ የሰው ልጆች ባሕርያት አንዱ ነው፡፡

ኢምቋ፡ ሰው መደነቅ ባሕሪ ብዙአለ አንድ ምን-እኔ አንተ ክብር- አንተ እኔ ክብር፡፡

3. አማርኛ፡ መከባበር ዓለማችንን የተሻለ መኖሪያ በማድረግ በኩል ከፍተኛ ሚና አለው፡፡

ኢምቋ፡ የእኛ ዓለም መሻሻል ጥሩ መኖር መሆን እኔ አንተ ክብር- አንተ እኔ ክብር ክፍታ አስተዋጽኦ አለ፡፡

4. አማርኛ፡ መከባበር በሁሉም ቦታ ለስኬታማነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

ኢምቋ፡ ሁሉም ቦታ ስኬት መምጣት ዋና አስፈላጊ ምን -እኔ አንተ ክብር- አንተ እኔ ክብር ፡፡

5. አማርኛ፡ በትምህርት ቤት ውስጥ በመምህራን፣ በተማሪዎች፣ በአስተዳደር ሠራተኞች እንዲሁም በወንዶችና በሴቶች መካከል መከባበር ሲኖር የመማር ማስተማሩ ሂደት የተሳካ ውጤቱም የሚያስደስት ይሆናል፡፡

ኢምቋ፡ ትምህርት ቤት አስተማሪ - ተማሪ ክብር - ክብር፣ መተዳደር ሠራተኛ እኔ ክብር- አንተ እኔ ክብር እንደገናወንድሴት እኔ አንተ ክብር- አንተ እኔ ክብር ውጤት ምን- መማር ማስተማር ስኬት ውጤት ጥሩ ደስ ደስ፡፡

## መልመጃ

መምህር፡ ይህን ክፍል የሚመለከተው የኢምቋ ጥናት ገና በሂደት ላይ ነው፡፡ የዚህ መልመጃ ዋንኛ ዓላማ ተማሪዎቹ የኢምቋ ትምህርትን ተምረው የጨረሱ እንዳይመስላቸውን ገና ወደ ፊት ለመማር የሚገባቸው ብዙ ትምህርት እንዳለ እንዲረዱና ለዚሁ እንዲነሳሱ ለማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎቹ መልመጃውን እንዲሞክሩ ከማበረታታት ባለፈ ትክክለኛ መልስ እንዲሰጡ የግድ አይበሏቸው፡፡ በማንኛውም ፈተና ውስጥም አያካቱት፡፡

በምዕራፍ ስድስት ውስጥ በተማሩት መሠረት ከላይ የተሰጡት የኢምቋ ናሙና ሰዋስው ውስጥ የሚገኙትን የባለቤት ማሳያ ምልክቶችእንዲያሳዩ ተማሪዎቹን ያበረታቷቸው፡፡

# ምዕራፍ ስምንት
# ወጣትነት

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

* የወጣትነት ባሕርያትን ያስረዳሉ፡፡
* በወጣትነት ዕድሜ ላይ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን ይዘረዝራሉ፣ ተግዳሮቶቹን እንዴት መያዝ እንዳለባቸውም ያስረዳሉ፡፡
* በወጣቶች ጉዳይ ላይ የሚቀርቡ የሚዲያ ፕሮግራሞችን ተከታትለው ሐሳቡን ያስረዳሉ፡፡
* ጅምር ዐረፍተ ነገሮችን ያጠናቅቃሉ፣
* በዐረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኙ ባዶ ቦታዎችን ይሞላሉ፣
* በሥርዓት ይወያያሉ፣
* የምልክቶች ትንተናና የሰዋስው እውቀታቸውን ያሳድጋሉ፣
* መስተዋድድ ምን እንደሆነ ተረድተው በኢምቋ ውስጥ እንዴት እንደሚገለጽ ያስረዳሉ
* መልመጃዎችን በመመሪያው መሠረት ይሠራሉ፡፡

የሚያስፈልገው ክፍለ ጊዜ ብዛት፡ ዘጠኝ ክፍለ ጊዜያት

*መርጃ መሣሪያዎች*

- የኢምቋ መዝገብ ምልክት
- የዘመኑን ወጣቶች የተለያዩ የሕይወት ዘይቤዎች የሚያሳዩ ፎቶዎች ወይም ምስሎች

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### መልመጃ አንድ፡ ዕይታዊ ንባብ

*የዚህ መልመጃ ዓላማ የምዕራፉን ቁልፍ ምልክቶች ለማስተዋወቅ እንደሆነ ያስታውሱ፡፡*

- *ሥዕሉን* በጥንቃቄ አጥንተው መልስ በመስጠት እንዲሳተፍ ተማሪዎቹን ያበረታቷቸው፤
- የተማሪዎቹ መልስ እንደ ተማሪው አመለካከት ሊለያይ ይችላል፡፡ ትኩረቱ የምልክት አጠቃቀማቸው ላይ ይሁን፤
- ተማሪዎቹ መልስ በሚሰጡበት ጊዜ የሚጠቀሙባቸውን ምልክቶች ወካይ ቃላት በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይጻፉ፤
- በውይይቱ መጨረሻ ላይ ከቁልፍ ምልክቶቹ ውስጥ ያልተጠቀሰ ካለ እርስዎ በዝርዝሩ ላይ ይጨምሩ፤
- ከተማሪዎቹ ጋር በመሆን ምልክቶቹን ከጣት ፊደላቸው ጋር ይድገሙ፡፡

### መልመጃ ሁለት

መምህር/ት ተማሪዎቹ በሥዕሉ ላይ የሚታዩትን ሁለት የወጣቶች ቡድን በማነጻጸር አምስት የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮች እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ምንባብ

*ምንባቡን ከማንበብዎ በፊት የሚከተሉትን ያከናውኑ፤*

- ቀደም ብለው የተዘጋጁትን የምንባቡን ቁልፍ ምልክቶች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጽፎ አሠራራቸውን ማሳየት፣ ጽንሰ ሐሳባቸውን ማስረዳት፡፡ ዝርዝሩ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤
    - ወጣትነት
    - ጎልማሳነት
    - ተግዳሮት
    - እውን
    - ማኅበራዊ
    - ሆርሞኖች
    - ባህሪ
    - በጠባይ
    - ተጽእኖ
    - ማኅበረሰብ
    - አደንዛዥ ዕፆች
    - አልኮልና
    - የሚያነቃቁ
    - ጉጉት
    - መደበር
    - ደንብ
    - መጣስ
    - ብልሀት
    - ፖለቲካዊ
    - ኢኮኖሚያዊ

*ከላይ የተቀመጡትን ምልክቶች ካሳዩ በኋላ፤*

- ለቁልፍ ምልክቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት ምንባቡን ለተማሪዎቹ ማንበብ፤
- የምንባቡን ሐሳብ የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮችን በመጠቀም ማቅረብ፤
- ተማሪዎቹ ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች እንዲጠይቁ ማበረታታት፤
- ተማሪዎቹ ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ትምህርት ዝግጅት ምንባቡን በግላቸው አንብበው እንዲመጡ ማበረታታት፡፡

## መልመጃ አንድ

ጥያቄዎቹ ተማሪዎቹ ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ምልክቶች አጠቃቀም ግንዛቤያቸውን ለማስፋት ታስበው የተዘጋጁ ስለሆኑ በክፍል ውስጥ በኢምቀ እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

1. እያንዳንዱ ተማሪ ከምንባቡ ውስጥ አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ በክፍል ውስጥ በኢምቋ እንዲያቀርብ ያድርጉ፡፡
2. ተማሪዎቹ የምንባቡን መልዕክት በአጭሩ በራሳቸው አቀራረብ በክፍሉ ወስጥ በኢምቋ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

## መልመጃ ሁለት

የመልመጃው መልሶች

1. ወጣትነት በልጅነትና በጎልማሳነት የዕድሜ ክልሎች መካከል የሚገኘው የዕድሜ ክልል ነው፡፡
2. ወጣትነትን ከሌሎች የዕድሜ ክልሎች የሚለየው በብዙ ተስፋዎችና ተግዳሮቶች የተሞላ የዕድሜ ክልልና የሕይወት አቅጣጫን የሚቀይሩ ብዙ ውሳኔዎች የሚወሰኑት በዚህ የዕድሜ ክልል መሆኑ ነው፡፡
3. ወጣትነትን ልዩ የሚያደርጉት የሚከተሉት ናቸው፤
   - በብዙ ተስፋዎችና ተግዳሮቶች የተሞላ የዕድሜ ክልል መሆኑ፣
   - የሕይወት አቅጣጫን የሚቀይሩ ብዙ ውሳኔዎች የሚወሰኑት በዚህ የዕድሜ ክልል መሆኑ፣
   - የሚከሰቱ አካለዊ፣ ስሜታዊ እና ማኅበራዊ ለውጦች መኖራቸው
   - ሆርሞኖች በባህሪ እና በጠባይ ላይ የሚፈጥሩት ተጽእኖ መኖሩ

- የማኅበራዊና ስሜታዊ ለውጦች መኖር፣ ወዘተ፡፡

4. መልሱ የሚከተሉተን ያጠቃልላል፤

- ራስን ስለመቻል ማሰብና ለራስ መወሰንን መሞከር ወይም መጀመር፣
- ስለወሲብ፣ አደንዛዥ እጾች፣ አልኮልና የሚያነቃቁ ነገሮችን የማወቅ እንዲሁም የመሞከር ጉጉት መጨመር፣
- የአቻ ጓደኞችን ምክር ከቤተሰቦች ምክር አስበልጦ መውሰድ፣
- ስለአለባበስ፣ አነጋገር፣ ራስን ስለመጠበቅ መጨነቅ መጀመር፣
- ስለ ውበት መጠንቀቅ፣
- ፈጣን የሆነ የባህሪ መቀያየር መኖር (ለምሳሌ አንድ ግዜ መደበር፣ መደሰት፣ መጨነቅ ወዘተ)፣
- የማኅበረሰቡን ደንብ፣ ፈቃድና ህጎችን መጣስና በቤተሰብ፣ በአስተማሪና በአዋቂዎች የተከለከሉ ተግባራት ለመፈጸም መሞከር፣
- በአካላዊ፣ ማኅበራዊና ስሜታዊ ለውጦች ምክንያት የሚፈጠሩ ፍላጎቶችን ጥቅምና ጉዳት የማመዛዘን እና የመረዳት ችሎታ አለመኖር፡፡

5. በወጣትነት ወቅት ራስን ከጎጂ ልማዶች በመጠበቅ፣ ራስን በእውቀትና በክሂሎት በመገንባት በሀገር ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ውስጥ ንቁ ተሳታፊ መሆን፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሦስት፡ የቡድን ሥራ

### መልመጃ አንድ

መምህር/ት፣

ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋፈል በአካባቢያቸው ወጣቶች ህይወታቸውን በሚመሩበት መንገድና መወሰድ በሚገባቸው እርምጃዎች ላይ እንዲወያዩና የውይይታቸውን ውጤት በተወካያቸው በኩል ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያስረዱ ያድርጉ፡፡

### መልመጃ ሁለት፡ ዐረፍተነገር ግንባታ

መምህር/ት፡

እንደተለመደው በመጀመሪያ ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡትን ቃላት ምልክቶች ያሳዩ፡፡ የምልክቶቹን

ጽንሰ ሐሳብም ያስረዱ፡፡ ቀጥሎ ተማሪዎቹ ምልክቶቹን በተለያዩ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ እየተጠቀሙ እንዲያሳዩ ያበረታቷቸው፡፡

1. ጎልማሳነት
2. ተግዳሮት
3. ተጽእኖ
4. አደንዛዥ ዕፆች
5. አልኮል

## መልመጃ ሦስት፡ የምልክቶች ተቃራኒ ማሳየት

የመልመጃው መልሶች

ምሳሌ፡

ሽምግልና፡ ልጅነት

1. የጎልማሳነት ምልክት
2. የማፍዘዝ ምልክት
3. የሞኝንት ምልክት
4. የግዴለሽ ምልክት
5. የድል ምልክት

## መልመጃ አራት

ባዶ ቦታዎችን መሙላት

1. በልጅነት እና በጎልማሳነት ወጣትነት
2. ተስፋዎች እና ተግዳሮቶች
3. የሕይወት አቅጣጫን
4. አካላዊ፣ የማኅበራዊና ስሜታዊ
5. ስኬታማ

## ክፍለ ትምህርት አራት፡ የምልክቶች ትናንሽ ክፍሎች ትንተና

ምሳሌ- ወጣት



| | | |
|---|---|---|
| 1. | የእጅ ቅርጽ፡ | የታጠፈ ገ |
| 2. | የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ፡ | ከጡቶች ግራ እና ቀኝ |
| 3. | የመዳፍ አቅጣጫ፡ | ወደ ውስጥ |
| 4. | የእጅ እንቅስቃሴ፡ | ከውስጥ ወደ ውጭ |
| 5. | በእጅ የማይገለጹ ክፍሎች፡ | ፈገግ ያለ ፊት |

## ክፍለ ትምህርት አምስት፡ የኢምቋ ሰዋስው ናሙናዎች

1. አማርኛ፡ “የወጣቶች አህጉር” በምትባለው አፍሪካ በቅርቡ በተካሄደው ጥናት 300 ሚሊዮን ያህል ወጣቶች አሉ፡፡

   ኢምቋ፡ ቅርብ ጥናት ተደረገ አሳየ ምን-አፍሪካ ውስጥ ወጣት ስንት 300 ሚሊዮን፡፡

2. አማርኛ፡ ከኢትዮጵያ ኅዝብ ውስጥ እስከ 37 ሚሊዮን ገደማ የሚሆነው የሀገሪቱ ዜጋ በወጣትነት ዕድሜ የሚገኝ ነው፡፡

   ኢምቋ፡ ኢትዮጵያ ኅዝብ ውስጥ ወጣት ስንት-ግምት 37 ሚሊዮንአካባቢ፡፡

3. አማርኛ፡ ወጣትነት አንድ ሰው ምን ለመሆን የሚወስንበት ብቻ ሳይሆን ውሳኔውን እውን ለማድረግ በሙሉ ኃይል ወደ ተግባር የሚገባበት ዕድሜ ነው፡፡

   ኢምቋ፡ ወጣት ዕድሜ ግዜ ማድረግ ምን- አንድ- ትልቅ መሆን መወሰን-ሁለት -ሃይል ሙሉ ተግባር መጀመር ግዜ፡፡

4. አማርኛ፡ በወጣትነት የሚወሰዱ እርምጃዎች በመጪው የሕይወት ዘመን ወሳኝ

ናቸው፡፡

ኢምቋ፡ ወጣት ዕድሜ ግዜ ውሳኔ ወደፊት ሕይወት ቁልፍ፡፡

5. አማርኛ፡ ወጣትነት በትግልና በፈተና የተሞላ እንዲሁም ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ የዕድሜ ክልል ነው፡፡

ኢምቋ፡ ወጣት ዕድሜ ግዜ ትግል ፈተና ብዙ ብዙ- እንደገና ጥንቅቅ ጥንቅቅ አስፈላጊ ዕድሜ ግዜ፡፡

## መልመጃ፡ መስተዋድድ

መስተዋድድ በስም ወይም ስምን መስለው በሚገኙ ቃላት ላይ እየተጫነ ገብቶ በዐረፍተ ነገር ውስጥ የንግግርን ዝምድና የሚያሳይ ቃል ነው፡፡ የመስተዋድድ ትርጓሜ አስማሚ ወይም አዋሃጅ እንደ ማለት ነው፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ

# የአየር ንብረት ለውጥ

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

* የወጣትነትን ባሕርያት ያስረዳሉ፡፡
* የአየር ንብረት ምንነትን፣ የአየር ንብረት መዛባትንና ብክለትን በተመለከተ ያገኙትን ግንዛቤ ይናገራሉ፡፡
* የውይይት ሥርዓት ጠብቀው ይወያያሉ፡፡
* ቃለ-ጉባኤ ይይዛሉ፡፡
* የስምና የግስ ገላጮችን፣ መስተዋድድንና ተውሳከ ግስን ከሚቀርቡላቸው ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ እየለዩ ያሳያሉ፡፡
* መረጃዎች ያሰባስባሉ፣ ያገኙትንም መረጃ በኢምቋ ያቀርባሉ፡፡
* የዐረፍተ ነገርን ክፍሎች ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ በማለት ይለያሉ፡፡
* ስለ መስተዋድድ ግንዛቤ ይጨብጣሉ፡፡

የሚያስፈልገው ክፍለ ጊዜ ብዛት፡ ስምንት ክፍለ ጊዜያት

መርጃ መሣሪያዎች

- የኢምቂ መዝገብ ምልክት
- የአየር ለውጥ ተጽእኖዎችን የሚያሳዩ ፎቶዎች ወይም ምስሎች

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### መልመጃ አንድ፡ ዕይታዊ ንባብ

*የዚህ መልመጃ ዓላማ የምዕራፉን ቁልፍ ምልክቶች ለማስተዋወቅ እንደሆነ ያስታውሱ፡፡*

- ሥዕሉን በጥንቃቄ አጥንተው መልስ በመስጠት እንዲሳተፉ ተማሪዎቹን ያበረታቷቸው
- የተማሪዎቹ መልስ እንደ ተማሪው አመለካከት ሊለያይ ይችላል፡፡ ትኩረቱ የምልክት አጠቃቀማቸው ላይ ይሁን፡፡
- ተማሪዎቹ መልስ በሚሰጡበት ግዜ የሚጠቀሙባቸውን ምልክቶች ወካይ ቃላት በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይጻፉ፡፡
- በውይይቱ መጨረሻ ላይ ከቁልፍ ምልክቶቹ ውስጥ ያልተጠቀሰ ካለ እርስዎ በዝርዝሩ ላይ ይጨመሩ፡፡
- ከተማሪዎቹ ጋር በመሆን ምልክቶቹን ከጣት ፊደላቸው ጋር ይድገሙ፡

## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ምንባብ

*ምንባቡን ከማንበብዎ በፊት የሚከተሉትን ያከናውኑ፤*

- ቀደም ብለው የተዘጋጁትን የምንባቡን ቁልፍ ምልክቶች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጽፎ አሠራራቸውን ማሳየት፣ ጽንሰ ሐሳባቸውን ማስረዳት፡፡ ዝርዝሩ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤
  - የአየርንብረት
  - ለውጥ

- በሂደት
- ሥጋት
- ሊያሳድር
- በተጨባጭ
- እየተከሰተ
- ክምችት
- ለመተንበይ
- አዳጋች
- መመናመን
- የሥነምሕዳር
- ተፅዕኖ
- መፈናቀል
- ሴክተሮች
- የልቀት
- የሚያባብሱ
- ካርቦን
- ቴክኖሎጂ
- መጨፍጨፍ

*ከላይ የተቀመጡትን ምልክቶች ካሳዩ በኋላ፤*

- ♦ ለቁልፍ ምልክቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት ምንባቡን ለተማሪዎቹ ማንበብ፣
- ♦ የምንባቡን ሐሳብ የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮችን በመጠቀም ማቅረብ፣
- ♦ ተማሪዎቹ ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች እንዲጠይቁ ማበረታታት፣
- ♦ ተማሪዎቹ ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ትምህርት ዝግጅት ምንባቡን በግላቸው አንብበው እንዲመጡ ማበረታታት፡፡

## መልመጃ አንድ

ጥያቄዎቹ ተማሪዎቹ በምንባቡ ውስጥ የተማሯቸውን ምልክቶች ለመለማመድና ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ምልክቶች አጠቃቀም ግንዛቤያቸውን ለማስፋት ታስበው የተዘጋጁ ስለሆኑ በክፍል ውስጥ በኢምቋ እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

1. እያንዳንዱ ተማሪ ከምንባቡ ውስጥ አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ በክፍል ውስጥ በኢምቋ እንዲያቀርብ ያድርጉ፡፡
2. ተማሪዎቹ የምንባቡን መልዕክት በአጭሩ በራሳቸው አቀራረብ በክፍሉ ወስጥ በኢምቋ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

## መልመጃ ሁለት

የመልመጃው መልሶች

1. የዓለም የአየር ንብረት ለውጥ ማለት ከተፈጥሮ የሁኔታዎች መለዋወጥ ወይም ከሰዎች ተግባራት የተነሳ በሂደት በአየር ንብረት ላይ የሚከሰት ለውጥ ማለት ነው፡፡
2. በተለምዶ ጭስ የሚባሉት የግሪን ሀውስ ጋዞች ክምችት በከባቢ አየር ውስጥ እንዲጨምር ከሚያደርጉ የሰዎች ተግባራት የተነሳ የሚከሰት ሁኔታ ነው፡፡
3. የአየር ንብረት ለውጥ የሙቀት መጠን እንዲጨምር፣ የባህር ጠለል ከፍ እንዲል፣ የአየር ጠባይ እንዲለዋወጥ፣ እንዲሁም ለመተንበይ አዳጋች የሆኑ ሌሎች ከባድ የአየር ጠባይ የመለዋወጥ ሁኔታዎች እንዲከሠቱ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም የዝናብ ሥርጭት ለውጦች፣ የጎርፍ ክስተቶች፣ የድርቅ ወቅቶች፣ ተደጋጋሚ የሠደድ እሣት አደጋዎች፣ የውሃ አቅርቦት መመናመን፣ ወዘተ እንዲፈጠሩ ያደርጋል፡፡

   የእነዚህ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖዎች ድምር ውጤትም የሰዎች ተጋላጭነት መጨመር፣ የግብርና ምርቶች መቀነስ፣ የምግብ ዋስትና አለመኖር፣ የውሃ አቅርቦት ችግር መባባስ፣ የሥነ ምህዳር መጎዳትና የጤና ችግሮች መስፋፋት ይሆናል፡፡
4. በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች በተለይም በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ለደርቅ ይጋለጣሉ፡፡
5. በአብዛኛው በአየር ንብረት ሁኔታዎች ላይ የተመረኮዙ የኢኮኖሚ ዘርፎች (ለምሳሌ ግብርና) ላይ በከፍተኛ ደረጃ የተመሠረቱ በመሆናቸው

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## መልመጃ አንድ፡ የቡድን ሥራ

መምህር/ት፣

እስካሁን ባሉት ክፍሎች በተሰጠው ትምህርት ስለ አየር ለውጥ ምንነትና ምልክቶች ተማሪዎቹ በቂ ግንዛቤ ጨብጠዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ የጨበጡትን ግንዛቤ መሠረት በማድረግ በቡድን በመከፋፈል በአካባቢያቸው የተመለከቱትን በአየር ንብረት ለውጥ የመጡ ችግሮች ላይ እንዲወያዩና የችግሮቹን ዝርዝር እንዲያዘጋጁ ያድርጉ፡፡ ቀጥለው መወሰድ የሚጋባቸውን እርምጃዎች ዝርዝር እንዲያዘጋጁ ያድርጉ፡፡ በመጨረሻም የውይይታቸውን ውጤት በተወካያቸው በኩል ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያስረዱ ያድርጉ፡፡

## መልመጃ ሁለት፡ ዐረፍተ ነገር ግንባታ

መምህር/ት፣

እንደተለመደው በመጀመሪያ ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡትን ቃላት ምልክቶች ያሳዩ፡፡ የምልክቶቹን ጽንሰ ሐሳብም ያስረዱ፡፡ ቀጥሎ ተማሪዎቹ ምልክቶቹን በተለያዩ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ እየተጠቀሙ እንዲያሳዩ ያበረታቷቸው፡፡

1. ሥጋት
2. መተንበይ
3. መመናመን
4. ተፅዕኖ
5. መፈናቀል

## መልመጃ ሦስት፡ ባዶ ቦታዎችን መሙላት

የመልመጃው መልሶች

1. የዓለም የአየርን ብረት ለውጥ
2. ኢኮኖሚና፣ ጤና ፣ ኑሮ

3. ጭስ፣ የግሪን ሀውስ ጋዞች

4. ጠለል ከፍ እንዲል፣

5. የዓለም የሙቀት

## ክፍለ ትምህርት አራት፡ የምልክቶች ትንተና

ምሳሌ፡

አየር



1. የእጅ ቅርጽ፡ አ
2. የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ፡ በደረት ፊት ለፊት
3. የመዳፍ አቅጣጫ፡ ወደ ግራ
4. የእጅ እንቅስቃሴ፡ ዝግዛግ
5. በእጅ የማይገለጹ ክፍሎች፡ ዘና ለ ፊት

## ክፍለ ትምህርት አምስት፡ የኢምቋ ሰዋስው ናሙናዎች

1. አማርኛ፡ የዓለም የአየር ንብረት ለውጥ ማለት በአየር ንብረት ላይ የሚከሰት ማንኛውም ለውጥ ማለት ነው፡፡

   ኢምቋ፡ ዓለም አየር ጠባይ ለውጥ ለውጥ ማለት ምን- አየር ጸበይ የተለያየ መሆን መለወጥ ማለት፡፡

2. አማርኛ፡ የአየር ንብረት ለውጥ በተጨባጭ እየተከሠተ ያለ ነገር ነው፡፡

   ኢ.ምቋ፡ አየር ጠባይ ለውጥ ለውጥ እውነት አለ አሁን፡፡

3. አማርኛ፡ የአየር ንብረት ለውጥ በዓለም ኢኮኖሚና በአካባቢ እንዲሁም በሠው ልጆች ጤና እና ኑሮ ላይ ከባድ ችግር ያስከትላል፡፡

   ኢ.ምቋ፡ አየር ጠባይ ለውጥ ለውጥ ችግር ብዙ ብዙ ኢኮኖሚ፣ አካባቢ፣ ሰው ኑሮ፣ ጤና ጉዳት ከባድ፡፡

4. አማርኛ፡ በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት በዋናነት የሚጎዱት በማደግ ላይ ያሉ ሀገሮች ናቸው፡፡

   ኢ.ምቋ፡ አየር ጠባይ ለውጥ ለውጥ ጉዳት ዋና ማን- ገና እድገት አገር፡፡

5. አማርኛ፡ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ሁላችንም የበኩላችንን ድርሻ መጣት አለብን፡፡

   ኢ.ምቋ፡ አየር ጠባይ ለውጥ ለውጥ መከላከል እኛ ሁሉም ራስ ራስ ድርሻ መሥራት ግዴታ፡፡

## መልመጃ

ተማሪዎቹ እስካሁን የተማሩትን መሠረት በማድረግ፣ ከላይ ከተሰጡት የኢ.ምቋ ሰዋስው ውስጥ የስምና የግስ ገላጮችን መስተዋድድንና ዐረፍተ ነገሮች ለይተው እንደያሳዩ ያድርጉ፡፡

# ምዕራፍ አስር
# የሀገር ፍቅር

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

* ስለ ሀገር ፍቅር ምንነትና አስፈላጊነት በኢምቋ ያብራራሉ፡፡
* የሀገር ፍቅር መግለጫ መንገዶችን ያስረዳሉ፡፡
* በአካባቢያችሁ ሰዎች ለሀገራቸው ያላቸውን ፍቅር ለማሳየት የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ለይተው ይገልጻሉ፡፡
* ሀገርን መውደድ ያለውን ጠቀሜታ በክፍል ውስጥ ይወያያሉ፡፡
* ሀገራቸውን መውደዳቸው የተመሰከራላቸው ኢትዮጵያውያን ታሪክ ከቤተ መጻሕፍት ፈልገው ታሪኩን በክፍል ጓደኞቻቸው ፊት ያቀርባሉ፡፡
* የኢምቋ ዐረፍተ ነገር ክሂሎታቸውን ያሳድጋሉ፡፡
* የምልክቶች ትንተና እና የሰዋስው እውቀታቸውን ያሳድጋሉ፡፡

የሚያስፈልገው ክፍለ ጊዜ ብዛት፡ *አሥራ አንድ ክፍለ ጊዜያት*

*መርጃ መሣሪያዎች*

- የኢምቋ መዝገብ ምልክት
- በሕይወት የሌሉ ነገር ግን ለሀገራቸው ስላላቸው ፍቅር የተጻፈላቸው ኢትዮጵያዋያን ፎቶዎች ወይም ምስሎች (ለምሳሌ አጼ ቴዎድሮስ፣ አጼ ዩሐንስ ወዘተ)

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### መልመጃ አንድ፡ ዕይታዊ ንባብ

*የዚህ መልመጃ ዓላማ የምዕራፉን ቁልፍ ምልክቶች ለማስተዋወቅ እንደሆነ ያስታውሱ።*

- ሥዕሉን በጥንቃቄ አጥንተው መልስ በመሰጠት እንዲሳተፍ ተማሪዎቹን ያበረታቷቸው።
- የተማሪዎቹ መልስ እንደተማሪው አመለካከት ሊለያይ ይችላል። ትኩረቱ የምልክት አጠቃቀማቸው ላይ ይሁን።
- ተማሪዎቹ መልስ በሚሰጡበት ግዜ የሚጠቀሙባቸውን ምልክቶች ወካይ ቃላት በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይጻፉ።
- በውይይቱ መጨረሻ ላይ ከቁልፍ ምልክቶቹ ውስጥ ያልተጠቀሰ ካለ እርስዎ በዝርዝሩ ላይ ይጨመሩ።
- ከተማሪዎቹ ጋር በመሆን ምልክቶቹን ከጣት ፊደላቸው ጋር ይድገሙ፡

## ክፍለ ትምህርት ሁለት፡ ምንባብ

*ምንባቡን ከማንበብዎ በፊት የሚከተሉትን ያከናውኑ፤*

- ቀደም ብለው የተዘጋጁትን የምንባቡን ቁልፍ ምልክቶች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጽፎ አሠራራቸውን ማሳየት፣ ጽንሰ ሐሳባቸውን ማስረዳት። ዝርዝሩ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤

- የሀገርፍቅር
- ሕያው
- ማኅተም
- ድንቅ
- መካድ

*ከላይ የተቀመጡትን ምልክቶች ካሳዩ በኋላ፤*

- ለቁልፍ ምልክቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት ምንባቡን ለተማሪዎቹ ማንበብ
- የምንባቡን ሐሳብ የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮችን በመጠቀም ማቅረብ
- ተማሪዎቹ ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች እንዲጠይቁ ማበረታታት
- ተማሪዎቹ ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ትምህርት ዝግጅት ምንባቡን በግላቸው አንብበው እንዲመጡ ማበረታታት

## መልመጃ አንድ

ጥያቄዎቹ ተማሪዎቹ በምንባቡ ውስጥ የተማሯቸውን ምልክቶች ለመለማመድና ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ምልክቶች አጠቃቀም ግንዛቤያቸውን ለማስፋት ታስበው የተዘጋጁ ስለሆኑ በክፍል ውስጥ በኢምቋ እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

1. እያንዳንዱ ተማሪ ከምንባቡ ውስጥ አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ በክፍል ውስጥ በኢምቋ እንዲያቀርብ ያድርጉ፡፡
2. ተማሪዎቹ የምንባቡን መልዕክት በአጭሩ በራሳቸው አቀራረብ በክፍሉ ወስጥ በኢምቋ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

## መልመጃ ሁለት

የመልመጃው መልሶች

1. የሀገር ፍቅር ዓለም አቀፋዊና ሁለንተናዊ መሆኑ
2. የሀገር ፍቅር በልብ ውስጥ እንደ ማኅተም ታትሞ የሚኖር ሕያው ስሜት ነው፡፡ እንደ ሐውልት በልባችን ውስጥ የሚታነጽ ዕፁብ ድንቅ ሕንፃ ነው፡፡

3. የማይነቃነቅ፣ ጠንካራ፣ የሚማርክ፡፡
4. ከማይጠፋ ሻማ፣ ከማይጠፋ ማኅተም፣ ከሚያብብ አበባ፣ ከማይነቃነቅ ሐውልት፣ ከሕንፃ
5. ሀገርና ራስ አንድ ናቸው ማለቱ ነው፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሦስት

### መልመጃ አንድ፡ የቡድን ሥራ

መምህር፣

ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋፈል ከሀገር ፍቅር ጋር ጋር ስለተያያዙ ጉዳዮች እንዲወያዩና ሪፖርት እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ ውይይቱ የሚከተሉተን ማጠቃለሉን ያረጋግጡ፤ የሀገር ፍቅር ምን እንደሆነ፣ እንዴት መግለጽ እንደሚገባን፡፡

### መልመጃ አንድ፡ የሚና ጨዋታ

*የሚና ጨዋታው የሚካሄደው በሚከተለው መንገድ ነው፤ በመጀመሪያ ተማሪዎቹ የሚከተለውን በቤታቸው ሠርተው እንዲያመጡ ያድርጉ፤*

- ተማሪዎቹ አንድ ሀገሩን መወደዱ የተመሰከረለት ኢትዮጵያዊ ይምረጡ (ለምሳሌ አጼ ቴውድሮስ፣ አጼ ዮሐንስ፣ አጼ ምኒሊክ፣ አብዲሳ አጋ፣ ደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶ፣ ወዘተ፣)
- ከተለያዩ መጻሕፍት ወይም ከሰው በመጠየቅ የመረጡት ሰው ሀገሩን በመወደዱ፣ ለማሳየት ያደረገውን  በደንብ ያጥኑና ማስታወሻ ይያዙ፣
- የመረጡትን ሰው በመምሰል ያደረገውን ሁሉ ማድረግ ይለማመዱ፡፡

### በክፍል ውስጥ፤

- በክፍል ጓደኞቻቸው ፊት የተለማመዱትን ያቅርቡ፣
- ሌሎች ጓደኞቻቸው የራሳቸውን ሲያቀርቡ በጥንቃቄ ተከታትለው አስተያየት ይስጡ ወይም ጥያቄ ይጠይቁ፡፡

### መልመጃ አንድ፡ ዐረፍተ ነገር ግንባታ

መምህር፣

እንደተለመደው በመጀመሪያ ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡትን ቃላት ምልክቶች ያሳዩ። የምልክቶቹን ጽንሰ ሐሳብም ያስረዱ። ቀጥሎ ተማሪዎቹ ምልክቶቹን በተለያዩ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ እየተጠቀሙ እንዲያሳዩ ያበረታቷቸው።

1. የሀገርፍቅር
2. ሕያው
3. ማኅተም
4. ድንቅ
5. መካድ

## ክፍለ ትምህርት አራት

### መልመጃ አንድ፡ የምልክቶች ተቃራኒ ማሳየት

የሚከተሉት ቃላት ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡ ናቸው። በቃላቱ የተወከሉትን ምልክቶች ተቃራኒ ምልክቶች በክፍል ውስጥ እንዲያሳዩ ያድርጉ።

1. የ ጥላቻ ምልክት
2. የ ሙት ምልክት
3. የ ማመን ምልክት
4. የ ማፍረስ ምልክት
5. የ ማጋለጥ ምልክት

### መልመጃ ሁለት፡ ባዶ ቦታዎችን መሙላት

የመልጃው መልሶች

1. የሐውልት ምልክት

2. የታሪክና የመካድ ምልክት
3. የአባቶችና የዘነጋ ምልክት
4. የ ባዕድ ምልክት
5. የ'ራሱንና የጠላ ምልክት

## መልመጃ ሦስት

**የመልመጃው መልሶች**

1. የግጥሙ መልዕክት፤ ሀገር የመቅደስን ያህል እጅግ የከበር በመሆኑ ታላቅ ክብር የሚገባው ነው የሚል ነው
2. ገጣሚው ሀገሩን ያመሳሰለው፤

   -ከመቅደስ፣ አድባር፣ አርማ፣ የነፃነት ዋንጫ፣ ታቦት፣ ለምለምና ውበት ጋር ነው።
3. ገጣሚው ለሀገሩ ያለው አመለካከት እጅግ የከበር አንድ ሰው ለፈጣሪው ያለው አይነት ፍቅርና አክብሮት ነው።
4. የኢትዮጵያን ባንዲራና ባንዲራው ያዘለውን ትርጉም ለማስገንዝብ ይመስላል። መምህር ጥያቄው ግምታቸውን እንዲናገሩ ስለሆነ ተማሪዎቹ የተለያየ መልስ ሊሰጠ ይችላሉ።
5. ይህን የሚጠቁመው የሚከተለው ነው፡

   ስሞት እሄዳለሁ ከመሬት ስገባ
   እዚያው ነው አፈሩ የማማ ያባባ።
   ስስብ እሄዳለሁ ቢሰበርም እግሬ
   አለብኝ ቀጠሮ ከትውልድ አገሬ

## ክፍለ ትምህርት አምስት፡ የምልክቶች ትንተና

**ምሳሌ፡**

**ፍቅር**



1. የእጅ ቅርጽ፡ የተጨበጡ እጆች
2. የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ፡ ደረት ላይ
3. የመዳፍ አቅጣጫ፡ ወደ ውስጥ
4. የእጅ እንቅስቃሴ፡ ከውጭ ወደ ውስጥ
5. በእጅ የማይገለጹ ክፍሎች፡ ፈገግ ያለ ፊት

## ክፍለ ትምህርት ስድስት፡ የኢምቋ ናሙና ሰዋስው

1. አማርኛ፡ የሀገር ፍቅር ስሜት ዓለም አቀፋዊና ሁለንተናዊ ነው፡፡

   ኢምቋ፡ ፍቅር ሀገር ስሜት ምን- ዓለም አቀፍ ሁሉም፡፡

2. አማርኛ፡ የሀገር ፍቅር ስሜት አንዱ ጋ በርቶ ሌላው ጋ የሚጠፋ ሻማ አይደለም፡፡

   ኢምቋ፡ ፍቅር ሀገር ስሜት እዚህ መብራት እዚያ መጥፋት ተመሳሳይ አይደለም ልዩ፡፡

3. አማርኛ፡ የሀገር ፍቅር በልብ ውስጥ እንደ ማኅተም ታትሞ የሚኖር ሕያው ስሜት ነው፡፡

   ኢምቋ፡ ፍቅር ሀገር ምን-ልብ ውስጥ ማህተም ተመሳሳይ መቀጠል መኖር፡፡

4. አማርኛ፡ አባቶቻችን እሾህ ሆነው ወራሪዎችን በመውጋት ሲመክቱ የኖሩት ለዚህ ነው፡፡

   ኢምቋ፡ አባት የእኛ ጠላት ጋር መዋጋት መዋጋት-መከላከል ምክንያት ምን- ይሄ፡፡

5. አማርኛ፡ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ለቅኝ ገዢዎች ፈፅሞ የማይመቹ ሆነው ኖረዋል፡፡

ኢምቋ፡ በፊት መጀመር አሁን ድረስ ኢትዮጵያ አገር እና እኛ ኀዝብ ጨቋኝ መመቸት አለመቻል መቀጠል፡፡

# የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ

## ፰ኛ ክፍል

የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር